# ጉባዔ

• የአገር ፍቅር • ታማኝነት • ሥራ

# የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ

መጋቢት 2008 ዓ.ም.

አርታኢ

**ሳምሶን ኃይሌ**

# መግቢያ

እንደሚታወቀው ቁሳራውያን ኃይሎችና ኢትዮጵያውያኑ ጠባብ ብሔረተኞች ከሚጋሯቸው አጀንዳዎች ውስጥ ሁሉም በአማራ ሕዝብ ላይ መዝመታቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ ቁሳራውያኑም ሆኑ ጠባብ ብሔርተኞች ቢቻል ‹‹ስለሕዝብ አንድነት ይሰብካል፤ ይዋጋል›› የሚሉት የአማራ ሕዝብ ቢጠፋላቸው ካለዚያ ደግሞ ጠባቦች እንደሚሉት አከርካሪውን ተመትቶ አንገቱን ደፍቶ ቢኖርላቸው ይወዳሉ፤ ለዚህም ያለማቋረጥ ይሠራሉ፡፡ ፋሽስቶች ሕዝቡን በቋንቋና በሃይማኖት በመከፋፈል ሁሉም አማራውን በጠላትነት እንዲፈርጀውና እንዲወጋው ያደረጉት ጥረት ሙሉ በሙሉ ተሳክቷል ባይባልም ከፍተኛ ውጤት እንዳስገኘላቸው ግን ግልጽ ነው፡፡ በፋሽስቶች ከፋፍለህ-ግዛ ስትራቴጂ ምክንያት አገሩን ከወራሪው ኃይል ለመከላከል የዘመተው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከትግራይና ራያ አካባቢ በወጡ ጠባብ ብሔረተኛና ጎጠኛ ኃይሎች ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰበት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ እንደነአዶልፍ ፓርለሳክና ኮ/ል አልኸንድሮ ዴል ባዬ ያሉ የውጪ ዜጎች ሳይቀሩ ምስክርነታቸውን የሰጡበት ጉዳይ ነው፡፡[1]

በዚያ የግፍ ዘመን ኢትዮጵያውያን ጀግኖች የሚዋጉት ሁለት ዓይነት ጦርነት ነበር፤ ከፋሽስት ወራሪ ኃይልና ከአገር ውስጥ ጎጠኞችና ጠባቦች ጋር፡፡ ጦርነቱ በፋሽስቱ ኃይል አሸናፊነት መጠናቀቁን ተከትሎ ኢትዮጵያውያን ማዕከላቸውን ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጎሬ ከተማ በማድረግ ጦርነቱን ለመቀጠል ወጥነው በሚንቀሳቀሱበት ወቅትም ቢሆን በጅማና አካባቢው የጠባብ ብሔረተኞች ጥቃት አልተለያቸውም ነበር፡፡[2] በአማራ ሕዝብ ላይ በጣሊያኖች የተጀመረው ዘመቻ በዘመናችን መልኩን ቀይሮና ተሻሽሎ በ‹‹አማራው ገዥ መደብ›› ስም ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡ ኦነጎች ለሥልጣን በበቁባት አጭር ጊዜ ውስጥ ከሕወሓትና ሻዕቢያ ጋር ተባብረው በዚህ ሕዝብ ላይ በበደኖ፣ በአርሲ፣ በወለጋና በሌሎች አካባቢዎች የፈጸሙትን ዘግናኝ እልቂት ማንም ሊረሳው አይችልም፡፡ እነዚህ ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶች ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ ወዘተ. እያሉ የሚወነጅሉት ‹‹ገዥ መደቡን ነው›› ይበሉ እንጂ ዓላማቸው ምንና በማን ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ በጣም ግልጽ ነው፡፡

---

[1] አልኸንድሮ ዴል ባዬ (ትርጉም- ተስፋዬ መኮንን ባይለየኝ) ፣ *ቀይ አንበሳ*፣ 1992 ዓ.ም. እና አዶልፍ ፓርካላስ (ትርጉም- ተጫነ ጆብሬ መኮንን) ፣ *የሐበሻ ጀብዱ*፣ 1989 ዓ.ም.

[2] የሀዲስ ዓለማየሁን *ትዝታ* እና *በምርኮ የተያዘ ሕዝብ* የሚለውን በበሪሁን አዳነ የተሰናኘ መጽሐፍ ይመለከቷል፡፡

አንድ አማራ በነፍጠኝነት ወይም በትምክህተኛነት የማይፈረጀው ሕወሓት/ኢሕአዴግንና ጠባቦችን እስካልተቃወመ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው። ይህን ካወቅን ቆይተናል። ለክብሩና ለነጻነቱ መታገል ከጀመረ ማንኛውም አማራ በትምክህተኛነትና በነፍጠኛነት ከመፈረጅ አያመልጥም።

ጠባብ ብሔረተኞች፣ የአማራ ሕዝብ የፊውዳሉን ሥርዓት በመቃወም ረገድ ከማንም በላይ የታገለና መስዋዕትነት የከፈለ ስለመሆኑ አይገልጹም። ስለነወልደአብ ወልደ ማርያም ትግል አብዝተው ይጽፋሉ። ስለቀዳማዊ ወያኔ ተጋድሎ ያለመታከት ይዘግባሉ። ስለነዋቆ ጉቱና ጀኔራል ታደሰ ብሩ ያወራሉ። የፊውዳሉን ሥርዓት በመቃወም ስለታገሉት ስለነዋይ ልጆች (መንግሥቱና ግርማሜ)፣ ስለኮ/ል ወርቅነህ ገበየሁና ስለጀኔራል ጽጌ ዲቡ፣ ስለ ታከለ ወልደሐዋርያት፣ ስለበላይ ዘለቀና ስለሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው የአማራ ልጆች ሊያነሱ አይፈልጉም። ስለሳልህ ሳቤ፣ እድሪስ አዋቴና ኢሳያስ አፈወርቂ ወዘተ. አብዝተው ይጽፋሉ። ስለመለስ ተክሌ፣ መለስ ዜናዊ ወዘተ. አበክረው ይዘግባሉ። ስለ ኢብሳ ጉተማ፣ ሌንጮ ለታ፣ ባሮ ቱምሳ ወዘተ. ይናገራሉ። ፊውዳሊዝምንና ጭቆናን ተቃውመው ስለተሰውት እጅግ ብዙ የአማራ ልጆች ግን ትንፍሽ አይሉም። የሚጠቅሱት አንድ የፈረደበት ዋለልኝ መኮንንን ብቻ ነው። ከዚያ አያልፉም። ይህም ያለምክንያት አይደለም። የፊውዳሉን ሥርዓት የአንድ ብሔረሰብ ሥርዓት ለማድረግና ‹‹ያን ሥርዓት ታግለን የጣልነው እኛ ጭቁኖች ነን›› ለማለት ነው፤ አማራውን አንደጨቋኝ ለመቁጠር ነው። ‹‹እናንተ ተጠቅማችኋል፤ አሁን ጊዜው የእኛ ነው›› ለማለት ነው። በክህደት የተሞላ ታሪክ ለመጻፍ ነው። ሌላው ሁሉ የዚህ ተቀጥላና ጭፍጫፊ ነው።

ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት በአማራ ሕዝብ ላይ ሲደርስ የቆየውና አሁንም የቀጠለው ውርጅብኝ እጅግ ዘግናኝ ነው። በአንድ በኩል የአማራ ሕዝብ በብዛት የሚኖርበትን አካባቢ ከውስጥም ከውጪም መቁረስና ቦታ ማሳጣት የተለመደ ድርጊት ሲሆን የሕዝቡ ቁጥር በፖለቲካ ውሳኔ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ መደረጉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል።

## የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ

ወልቃይት ትግራይን ለማጠናከር ብቻ ሳይሆን የአማራን ሕዝብ በሁለንተናዊ መልኩ ለማዳከም በተያዘው የረዥም ጊዜ ዕቅድ መሠረት ከአማራ ክልል በጠብመንጃ አፈሙዝ

ተነጥቆ የተወሰደ የአማራ መሬት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ስለወልቃይት ሕዝብ አማራነት ይህን ሕዝብ ላለፉት (ከሁለት ዐሥርት በላይ) ዓመታት ቀጥቅጦና በግፍ አስቃይቶ የሚገዛው የሕወሓት አመራርም ጠንቅቆ ያውቃል። አምስት እጅግ ሰፋፊ ወረዳዎችና ሦስት የከተማ አስተዳደሮችን ያቀፈው፣ እጅግ ለምና የአገራችን የሰሊጥ፣ ጥጥ፣ እጣን፣ ማርና የማሽላ ምርት ጎተራ የሆነውን የወልቃይትን መሬት ሕወሓት ገና ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ ሲቋምጥበት የነበረ ሲሆን፣ ሕወሓት የወልቃይትን ሕዝብ መብት ገፍፎ በአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ሥር ማስገባት የጀመረው ገና በአገር ደረጃ አሸናፊ ሳይሆን እንደነበር ሁሉም እንዲገነዘበው ያስፈልጋል።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ የሚማረርና የማንነት ጥያቄዎችም በየአካባቢው የሚነሱ የዘወትር አጀንዳዎች ቢሆኑም፣ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የደረሰው በደል ከሌሎች የአገራችን ሕዝቦች በደል በእጅጉ የተለየና ዘግናኝ ሆኖ ሳለ፣ የሕዝባችን ስቃይ በኢትዮጵያውያንና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚገባውን ትኩረት ሳያገኝ መቆየቱ እጅግ የሚያጠያይቅ ነው። የወልቃይት ሕዝብ ስቃይ የበዛውና ዕውቅና ተነፍጎት የቆየው በአንድ በኩል ጥያቄው በሥልጣን ማማ ላይ ካለው ከሕወሓት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሲሆን፣ በዋነኛነት ግን ጥያቄው የአማራ ሕዝብ ጥያቄ በመሆኑ፣ አማራው ደግሞ በሕወሓት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጠባብ ብሔርተኛ ድርጅቶች ዘንድ እንደጠላት የሚቆጠር ስለሆነ፣ የአማራ ጉዳት የሚያሳስበው ባለመሆኑ፣ እንዲያውም በዚህ ሕዝብ ጉዳት ደስ የሚሰኙ ኃይሎችም በመኖራቸውም ነው።

በግልጽ ሊታወቅ የሚገባው ዕውነታ፣ ሕወሓትና ሌሎች ጠባብ ብሔርተኛ ድርጅቶች በአማራ ሕዝብ ላይ ያሰራጩት የጥላቻ መርዝ ፍሬ አፍርቷል። በዚህ ምክንያት ከጥቂት አገር ወዳዶች ውጪ ለአማራ ሕዝብ የሚቆረቆር አማራ ያልሆነ አካል የለም። ለአማራ ሕዝብ ከራሱ ከአማራው ውጪ ሊቆምለት የሚችል እንደሌለ ከወልቃይት ሕዝብ ስቃይ በላይ አብነት የለም። አማሮች በአገራቸው ባይተዋር ሆነው ከየአካባቢው ሲባረሩና ሲገደሉ የጮኸላቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅት አለመኖሩ በራሱም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ጉዳይ ነው።

ደግነቱ አንድ የወልቃይት አባት ‹‹ወልቃይት ማለት ወሎ ነው፤ ጎጃም ነው፤ ሸዋ ነው፤ ጎንደር ነው›› ሲሉ በግልጽ ቋንቋ እንዳስቀመጡት፣ አሁን ሁሉም የአማራ ልጅ

የወልቃይትን ጥያቄ የራሱ ጥያቄ አድርጎ መንቀሳቀስ መጀመሩ እጅግ የሚያስደስትና ተስፋ የሚሰጥ ነው። ወጣቱ ‹‹የወልቃይት ሕዝብ መታሰር የእኛ መታሰር ነው፤ ሞታቸው ሞታችን ስቃያቸው ስቃያችን ነው›› እያለ ነው። ብዙዎችም [ከዚህ በታች የቀረቡትን ጨምሮ] በወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ ላይ መጻፍ ጀምረዋል። ይኼ ትልቅ ድል ነው። እንደዚህ ያለ መቆርቆርና በጋራ መቆም እስከተፈጠረ ድረስ የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ መቼም ቢሆን ሊዳፈን አይችልም። እንደዚህ ዓይነት ኅብረት ካለ የወልቃይትን ሕዝብ ወሳኝ የማንነት ጥያቄ አንዴ በመልካም አስተዳደር ችግር ስም፣ ሌላ ጊዜ በጸረ ሰላም ኃይሎች እንቅስቃሴ ስም ወዘተ. እያጭበረበሩ አቅጣጫውን ማስቀየር አይቻልም። የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄ የማንነት ጥያቄ ነው፤ አገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ የመላቀቅ ጥያቄ ነው።

# ሕወሓትና የወልቃይት ሕዝብ

ሳምሶን ኃይሌ

ከአንድ ሳምንት በፊት የወልቃይት አማሮች የማንነት ጥያቄ አስተባባሪዎቹ ሊያገኙኝ እንደሚፈልጉ ገልጸውልኝ በቀጠሯችን መሠረት ተገናኘንና፣ ለኢፌዴሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት ያስገቡትን የማንነት ጥያቄ ማመልከቻ እንዲሁም ከ116 በላይ የት እንደደረሱ የማይታወቁ ወገኖቻቸውን ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ሰጡኝ፡፡ ሰነዱ በራሱ ገላጭ ቢሆንም የአካባቢውን ተወላጆች መሠረታዊ ጥያቄ በሚገባ ለመረዳት በዕድሜና በተመክሮ በሳል የሆኑ ሰዎችን ማነጋገሩ የተሻለ መስሎ ስለተሰማኝ ሐሳቤን ገለጽኩላቸው፡፡ እነሱም ጥያቄየን ተቀብለው ከአንድ የ70 ዓመት አዛውንት ጋር አገናኙኝ፡፡

ያገኘዋኂቸው አባት ታሪክን ጠንቅቀው የሚያውቁ የቤተ ክህነት ሊቅ ናቸው፡፡ እኚህ አዛውንት ስለወልቃት ጠገዴ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵና ሱዳን ጉዳይ ላይ ያላቸው ዕውቀትም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የሚከተለው ጽሑፍ እኒህ የዕድሜ ባለጸጋ የወልቃይት ተወላጅ ካጫዎቱኝ ዝርዝር ነገር ውስጥ ተቀንጭቦ የቀረበ ነው፡፡ አዛውንቱ ይናገራሉ፡-

የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ወንዱም ሴቱም ጅግና ነው፡፡ በጣሊያን ወረራ ዘመን እናቶቻችን ልጆቻቸውንና ባሎቻቸውን አልጋ ሥር ጠመንጃ አቀባብለው እንዲደበቁ ያደርጋሉ፡፡ እነርሱ ደግሞ በርበሬ (ሚጥሚጣ) ድቁሱን በውኃ በጥብጠው ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚያም የጠላት ወታደር በውበታቸው ማርከው ወደ ቤት ያስገቡታል፡፡ የወልቃይቷን ሴት ውበት ዓይቶ በስስት የሚገባው ፈረንጅ ፊትና ዓይን ላይ ያን የተበጠበጠ በርበሬ ይደፉበታል፡፡ ያ ወታደር ሲደናበር አልጋ ሥር የተደበቀው ባለነፍጥ አናቱን ብሎ እየሸለለ የጠላትን ትጥቅ ቀምቶ ጫካ ይገባል፡፡

ኢሕአፓና ሕወሓት ታኅሣሥ 21 ቀን 1972 ዓ.ም. በወልቃይት ደጀና ከተባለ ቦታ ላይ ጦርነት ገጠሙ፡፡ ‹‹ግንብ›› የተባለ ጎድጓዳ ቦታ አለ፡፡ ግንብ ውስጥ ሰው ቢጮህ ማንም አይደርስለትም፡፡ ጥይት ቢተኮስም ርቀት ቦታ አይሰማም፡፡ ደጀና ላይ ሲዋጉ የነበሩ የኢሕአፓ ወታደሮች ሁሉ ግንብ ውስጥ ዶግ አመድ ሆኑ፡፡ አስከሬን ቀባሪ አጥቶ ለአሞራ ቀለብ ሆነ፡፡ የሰው ልጅ ለካ ያን ያክል ስብ ይሸከማል? ስቡ ቀልጦ የሚፈሰው መሬቱን ሁሉ አጥቁሮት ነበር፡፡ የጥይት ድምጽ አፍኖ የሚይዘው ግንብ አስከሬኖቹ የሚተፉትን መጥፎ ጠረን ግን አፍኖ መያዝ ተሳነው፡፡ ድፍን ወልቃይትን በመጥፎ ጠረን አሰከረው፡፡

ከሞት ያመለጡት የኢሕአፓ ሠራዊት አባላት ወደ ሱዳን ተሰደዱ። የወልቃይት ጠገዴ ጣዕር ከዚህ ጊዜ ይጀምራል። ሕወሓቶች ወልቃይት ጠገዴን ዙረው ሲመለከቱ በመሬቱ ለምነት ጎመጁ። በዚህ ምክንያት መሬቱን ለመውሰድ ሕዝቡን በልዩ ልዩ መንገድ ማሰቃየትና ከአካባቢው ማፈናቀልን ሥራዬ ብለው ተያያዙት። በዚህ መንገድ ሕወሓት ‹‹ኢሕአፓን አስጠልላችኋል›› በማለት በወልቃይት ሕዝብ ላይ መከራውን አንድ ብሎ ጀመረ። ያኔ የተጀመረው መከራ አሁንም ይበልጥ ተጠናክሮ ቀጠለ እንጂ አልቆመም። ኢሕአፓን አስጠግተዋል ያላቸውን አማሮችን ቤትና ንብረት ማቃጠል የጀመረው ሕወሓት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የወልቃይት ወጣቶችን ሰበብ እየፈለገ መግደል ሥራው ሆነ፤ የግፍ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ተጫነ። ለዚህ ደግሞ የሱዳን መንግሥት ታላቅ ሚና ተጫውቷል። አሁንም ቢሆን የሱዳን መንግሥት የጥፋት እጆች አልተሰበሰቡም።

የወልቃይት ጠገዴ አማሮች የተከፈተባቸው ጥቃት ሁለንተናዊና ከብዙ አቅጣጫ ነው። የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሥነ ልቦናዊ ጦርነት ሰላባ ናቸው። በመንግሥት መሥሪያ ቤት ቅድሚያ የሚሰጥ ከመሐል አገር ለሚመጣ የትግራይ ተወላጅ ነው። የወልቃይት ልጆች ትምህርት በአማርኛ መማር አይችሉም፤ ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ማውራትም አይችሉም። ክልክል ነው። ሕወሓት በዚያ አካባቢ መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከሰላሳ በላይ ለሚሆኑ ዓመታት የኢትዮጵያም ሆነ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ያላወቀ ብዙ በደል ደርሷል። አያሌ የወልቃይት ተወላጆች ተገድለዋል፤ ተሰደዋል። ቁጥራቸውን የማናውቀው ልጆቻችን የት እንደወደቁ ሳይታወቅ ደብዛቸው ጠፍቷል።

የሕወሓቶች ግፍ ወልቃይት ጠገዴ አማሮች የተፈጥሮ ስሜታቸውን እንኳ በወዱ እንዳይገልጹ ነው የሚያስገድዷቸው። የዳንሻ ከተማ ከንቲባ ሕዝቡን ሰብስቦ ‹‹ልጆቻችሁ ስለምን አማርኛ ያወራሉ!›› በማለት በአደባባይ ሕዝቡን ማስፈራራቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው። አማርኛ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ‹‹የኢሕአፓ ቅሪቶች›› በመባል ይታወቃሉ። አማርኛ የሚናገሩ ሰዎች ምንም ዓይነት መብት የላቸውም። የሕግ አካላት የአማራ ተወላጆችን አያስተናግዱም። የወልቃይት ተወላጆች ከትግራይ ብሔረሰብ አባላት ጋር ተጋጭተው ወይም ሌላ በደል ደርሶባቸው ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ቢያመለክቱ የፍትሕ አካሉ ለትግራዩ እንደሚያዳላ ማንም ያውቃል። የተለመደ ነው።

ትግርኛ በአግባቡ ባለመናገራቸው በደል የሚደርስባቸው የወልቃይት አማሮች ብዙ ናቸው። ለናሙና አንድ ሁነት እናንሳ። የአካባቢው ሕዝብ ባህሉም ሥነ ልቦናውም ምርጫው አማራነት ነው። ሕዝቡ ለትግራይና ኤርትራ ቅርብ በመሆኑ እንደሌሎች በአዋሳኝ አካባቢዎች እንደሚኖሩ ሕዝቦች የተለያየ ቋንቋ ይናገራል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በየትም አካባቢ ያለና ተፈጥሯዊ ነገር ነው። የድሬዳዋ ሕዝብ ከአማርኛ ሌላ ሶማሊኛም ኦሮምኛም እንደሚናገር ይታወቃል። ኢትዮጵያውያን በሌሎች የአገራችን ጥአካባቢዎችም እንዲሁ ነው። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብም ከአማርኛ ሌላ ትግርኛ ይናገራል። ዐረብኛ ቋንቋ የሚናገሩም ብዙዎች ናቸው። ሕዝቡ ትግርኛ ይናገር እንጂ የአካባቢው ትግርኛ የተለየ ነው። ወደ አማርኛ በእጅጉ ይቀርባል። የትግራይ ብሔረሰብ አባላት ይህን በሚገባ ያውቃሉ። በዚህ ምክንያትም ብዙ በደል አለ። ትምህርት ቤት ሞክሼ የአማርኛ ፊደላትን የሚጽፉ ተማሪዎች ካሉ በጣም ይወገዛሉ። ለምሳሌ ኀ፣ ሠና ፀ የአማርኛ ፊደላት ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ መምህራን ለፊደላቱ ያላቸው ጥላቻ የበዛ ነው። እንደሚታወቀው ጉራጌ ዞን ውስጥ ለምሳሌ ለኦሮሚያ ክልል ቅርብ በሆነው ሶዶ ወረዳ ውስጥ ብዙዎች ኦሮምኛ ቋንቋ ይችላሉ። ኦሮምኛ ስለሚናገሩ ኦሮሞ ናቸው በሚል ወደኦሮሚያ ክልል ለመጠቅለል ጥረት ቢደረግም ሕዝቡ ማንነቱን አሳልፎ አልሰጠም።

መታወቅ ያለበት የብሔረሰቦች መብት ተከብሯል እየተባለ ድቢ በሚመታበት ዘመን የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ያለታሪኩና ፍላጎቱ ወደትግራይ ክልል እንዲጠቃለል የተደረገው በሕወሓት ውሳኔ በመሣሪያ አፈሙዝ ነው። ሕዝቡ ፈጽሞ አልተጠየቀም፤ ሐሳቡን እንዲገልጽ ዕድልም አልተሰጠውም። አካባቢው በትግራይ ክልል ሥር እንዲሆን ከተወሰነ ጀምሮ የመብት ጥያቄ የሚያነሱ ልጆቻችንን ስንቀብር ኖረናል። ጥያቄው ወደፊት እንዳይቀርብና ለአንዴና ፋይሉን ለመጨረሻ ጊዜ ለመዝጋት ሲባል በሺህዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን በአያት ቅድመ አያቶቻችን ርስት ላይ በማስፈር የትግራይን የበላይነት ለመፍጠር ያልተሞከረ ነገር የለም። የሕዝባችን በደል ድርብ ድርብርብ ነው የምንልበት ምክንያት በደሉ በባለመሣሪያው ሕወሓት የሚፈጸም በመሆኑ እንደሌሎች ሕዝቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ እስካሁን ጎልቶ ባለመውጣቱ ነው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የተሻለ ሁኔታ ቢኖርም ከደረሰብን በደል ጋር ስናወዳድረው በጣም የሚያሳዝን ነው።

## የሱዳን መንግሥት ለኢትዮጵያ የአጥንት ቲቢ ነው!

የሱዳን መንግሥት እኮ ለአገራችን የአጥንት ቲቪ ነው፡፡ የሱዳን መንግሥት የወልቃይትን አማሮች ከሕወሓት ጋር እንዴት አድርገው እንደፈጇው በሚገባ እናውቃለን፡፡ ከ1972 ጀምሮ ሕወሓቶች አስቀድመው የሚያጠና ሰው ይልካሉ፡፡ ሰላይ መሆኑ ነው፡፡ አስቀድመው የሚመጡት ሰላዮች በራሱ መተማመን ያለውንና ቆይቶም ለሕወሓቶች ተቃውሞ ያነሳል የሚሉትን ወጣት በስም ዝርዝር ይልካል፡፡ ሕወሓቶች ለሱዳኖች ይናገራሉ፡፡ ሱዳኖች መኪና ይዘው ይገባሉ፡፡ ወጣቶቹን ይይዙና ወደ ግዛታቸው ይወስዷዋል፡፡ ‹‹ዛሬ እከሌ ጠፋ! ዛሬ እከሌ በሱዳኖች ተወሰደ!›› ሁልጊዜም የሚሰማ እሮሮ ነው፡፡ ይህ እሮሮ በሕወሓቶች የሽፍትነት ዘመን ብቻም ያቆመ አይደለም፡፡ እስካሁን ድረስ የቀጠለ ደረቅ ሐቅ እንጂ፡፡ ሱዳን ድንበር ከገቡ በኋላ በጥይት ተደብድበው ይገደላሉ፡፡ ትልልቅ ከተማዎች አደባባይ ላይ ይሰቀላሉ፡፡ ከተማ አደባባይ ላይ የሚሰቀሉትን በተመለከተ ሱዳኖቹ የሚሉት ‹‹ሐበሻ ራሱን አጠፋ›› ነው፡፡ ሕወሓቶች ራሳቸው የወልቃይት አማራ ወጣቶችን ጉድጓድ እንዲቆፍር ካደረጉ በኋላ በቆፈሩት ጉድጓድ ይቀብሯቸዋል፡፡ ‹‹የትግሬ እናት ሐዘን ተቀምጣ አንተ ጠግበህ ትበላለህ?›› በማለት ውኃ በቀጠነ ይገድሏቸዋል፡፡

ሕወሓቶች እንዲህ ይላሉ፤ ‹‹መሬቱ እንጂ ሕዝቡ አያስፈልገንም፡፡›› የሱዳን ዜጎች ድንበር አካባቢ የሚያገኟቸውን ኢትዮጵያውያን ሳይጠይቁ የማያልፉት ነገር አለ፡፡ ይኸውም ‹‹አማራ ነህ ትግሬ!›› የሚል ነው፡፡ ለሱዳኖች ሰው ማለት ትግሬ ነው፡፡ አማራ የሱዳን ጠላት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ የሱዳን ደህንነቶች የፈለጉትን የወልቃይት ተወላጅ በፈለጉት ጊዜ መጥተው መውሰድ ይችላሉ፡፡ የሕወሓትም ደህንነቶች እንዲሁ፡፡ የወልቃይት ተወላጆች ወደ ሱዳንም ቢገቡ እዚህ ቢቀመጡ ያው ነው፡፡ የወልቃይት ተወላጆችን ግፍ ሊያስረዳ የሚችል አንድ ምሳሌ እንጥቀስ፡፡ ቄስ ተገን እንየው የሚባል ካርቱም እስጢፋኖስ የሚያገለግል የወልቃይት አማራ አለ፡፡ ቄስ ተገን በቤተ ክህነት ትምህርት ከዚህ ቀረህ የማይባል ምሁር ነው፡፡ በግዕዝ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በዐረብኛ ደግሞ ከግብጥ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያኖች ይቀድሳል፡፡ ቄስ ተገን ያለውን ለአገሩ ልጆች አካፍሎ ይበላል፡፡ ሕወሓቶች ቄስ መስፍን አገር ውስጥ ላሉ ለሚማሩ ልጆች ገንዘብ እንደሚረዳ ደረሰቡት፡፡ ለተቸገረ ገንዘብ መለገስ የሚያስመሰግን እንጅ የሚያስወቅስ ሆኖ አልነበረም፡፡ ባለፈው መጋቢት ወር 2007 ዓ.ም. ካርቱም የተላከ የወያኔ ደህንነት ይዞት መጣ፡፡ ማዕከላዊ እስከ ጥቅምት 2008 ዓ.ም.

ከማንም ከምንም ጋር ሳይገናኝ ጨለማ ቤት አቆይተው ‹‹ለማንም እንዳትናገር›› ብለው ለቀቁት፡፡ ቄስ ተገን ምንም አማራጭ ስላልነበረው አሁን ወደ ካርቱም ተመልሷል፡፡

የወልቃይት ልጃገረዶች በትምህርት ቤት የሚደርስባቸው አበሳም ከፍተኛ ነው፡፡ ሐሙስ ሐሙስ ሴት ተማሪዎች የመምህራንን መኖሪያ ያጸዳሉ የሚባል ያልተጻፈ ሕግ ነበር፡፡ ገና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሕፃናት የመምህራኖቻቸውን ቤት ለማጽዳት በተራ ሁልጊዜ ሐሙስ ‹እነ ጋሽዬ› ቤት ይሄዳሉ፡፡ ሕፃናቱ በመምህራኖቻቸው ይደፈራሉ፡፡ ያረግዛሉ ይወልዳሉ፡፡ በሕግ ሊያገቡ የታጩ ልጃገረዶች ሁሉ እየተደፈሩ ያገባሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አማሮችን ትግራዊ ለማድረግ ብቻ ነው፡፡

የወልቃይት አባቶች ተጨነቁ፡፡ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ላለመላክ ወሰኑ፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ ለትምህርት የደረሰ ልጁን እቤት ያስቀመጠ ሰው ይቀጣል የሚል ሕግ መጣባቸው፡፡ ወላጆች አሁን ሌላ አማራጭ ፈለጉ፡፡ ‹በመምህራን› ልጆቻቸው ከመደፈራቸው በፊት በልጅነታቸው መዳር፡፡ መጨነቅ ነው፡፡ ይህም ሌላ ጣጣ አስከተለ፡፡ በሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ‹‹ያለ ዕድሜ ጋብቻ›› በሚል ክስ ይመሠረትባቸዋል፡፡ ያለ ዕድሜያቸው በሚደፍሯቸው መምህራን ላይ ግን ማንም ምንም አይልም፡፡ ይህ ሁሉ ችግር የሚደራረብባቸው ወልቃይቴዎች ያላቸው አማራጭ ሁለት ብቻ ነው፡፡ አንደኛው ልጆቻቸውን ወደ ጎንደርና ሌሎች አካባቢዎች ወስዶ ማስተማር ሲሆን ሁለተኛው ግን የመምህሮቹን ‹‹ዲቃላ›› ማሳደግ፡፡

መታወቅ ያለበት አንድ መሠረታዊ ነገር አለ፡፡ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ጥያቄ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ አይደለም፡፡ ይህ ማለት ሕዝቡ የመልካም አስተዳደር ችግር የለበትም ማለት አይደለም፡፡ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እንደሚታየው በእኛ አካባቢም የመልካም አስተዳደር ትልቅ የመልካም አስተዳደር ችግረ አለ፡፡ ይሁን እንጂ የእኛ ዐቢይ እና የሕወሓት ሰዎች የቱንም ያህል ቢገድሉንና ቢያሳድዱን የማንተኛለት፤ እኛ መፈጸም ባንችል ጉዳዩን ለልጅ ልጆቻችን የምናወርሰው ጥያቄ የማንነታችን ጉዳይ ነው፡፡ አማሮች ነን፡፡ ትግራይ አይደለንም፡፡ ሕወሓት ቱንም ያህን የትግራይ ተወላጅ በመንግሥትና በድርጅት በተመደበ በጀት አስፍሮ ከርስታችን ሊነቅለን ቢሞክርም ማንነታችን ማጥፋት አይችልም፤ ከርስታቸው የተፈናቀሉት ወገኖቻችንም በአማራ ልጆች ጥረት ይመለሳል፡፡ በዚህ ላይ ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለኝም፡፡

የሆነ ሆኖ የደረሰብንና እየደረሰብን ያለውን ያልተነገረ በደል ኢትዮጵያውያንና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲገነዘቡልን እንፈልጋለን። በዚህ ረገድ ሁሉም አገር ወዳድ ከእኛ ጋር እንደሚቆም እንጠብቃለን። ጥረታችን የልጆቻችን ሞትና ስቃይ እንዲያበቃ፤ ልጆቻችን በማንነታቸው ኮርተው በአያት ቅድመ አያቶቻቸው ርስት ላይ በሰላም የሞኖሩበት ዘመን እንዲመጣ ነው።

# ወልቃይት ጠገዴ

## የታላቅነት ቅዠት ሰለባ!

**አቶ ግዛቸው አበበ**

አንበሳው ወልቃይቴ ሲባል ሰምተው ያውቁ ይሆን? በእርግጥም አንበሳነት ለወልቃይት ጀግኖች የሚበዛባቸው አይደለም። ወልቃይቶች እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ነጻነትና ህልውና በጽናት የቆሙ ሰዎች ናቸው። ወልቃይቶች ልጆቻቸውን አተኳኮስ እያስተማሩ ማሳደጋቸው፣ የሰርግ ዘፈናቸው ‹‹አሆሆ ይሉሻል ገዳዪ!›› እንደመሆኑ መጠን ጀግንነት ሥራቸው ነው ማለት ይቻላል። ያም ሆኖ በዚያ አካባቢ ለጊዜው ወይም በቋሚነት ኀራ ላለ ሰው የሚያሳዩት ፍቅር ልዩ ነው። የወልቃይት ውኃ ሰው ያለምዳል ይባላል። ይህም ቦታው ለማንኛውም ከሌላ አካባቢ ለሚመጣ ሰው የሚስማማውና እዚያው እንዲኖር የሚገፋፋው፣ በተፈጥሮ የታደለው ለሙ የእርሻ መሬት ያረሰውን ሁሉ በተትረፈረፈ ፍሬ ባለጸጋ በማድረጉና ወልቃቴዎችም ኩሩ ሕዝቦች ቢሆኑም ሰው አክባሪዎች በመሆናቸው ነው።

አንቶኒ ሞክለር የተባለው ጸሐፊ ‹‹የኃይለሥላሴ ጦርነት›› በሚል ርእስ ባሳተመው መጽሐፍ ሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ያስከተለውን ጦርነት በሰፊው ይተርካል። አንቶኒ ሞክለር በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ብዙ አስገራሚ ነገሮችን አስፍሯል። ከነዚህ አስገራሚ ታሪኮች ውስጥ በወልቃትና በአርማጭሆ አካባቢዎች የተከሰቱ ጉዳዮች ይገኙበታል። በጣሊያን ወረራ ወቅት በአካባቢው ሰርግ ተደረገ፤ በሰርጉ ላይ የጦርነትና የጀግንነት ዘፈኖች ብቻ ነበረ የተዘፈኑት። ዕድሜያቸው የገፉ አባቶች ደርቡሽን በጎራዴ ያባረረው ሕዝብ አሁን ጠመንጃ ሞልቶለት የጣሊያኖች ጎረቤት ሆኖ እንዴት ይኖራል እያሉ የሰርጉን ዳስ ፉከራ በፉከራ አደጉት። አንቶኒ ሞክለር በዚያው ዕለት የተፈጸመውን ሲገልጸው ‹‹እድምተኞች ብቻ ሳይሆኑ ሙሽራውና ሚዜዎቹም እየፎከሩ አርበኞችን ለመቀላቀል ዱር ቤቴ አሉ›› ብሏል። የዚህ ዓይነቱ እውነታ ነው የወልቃትን ጠገዴን፣ የአርማጭሆን ነዋሪዎች ‹‹አንበሶች›› ያስባላቸው።

ይህን መሰሉን ታሪክ መዘከር ያስፈለገው ሰሞኑን በኢቢሲው የትግርኛ ቴሌቪዥን የማንነት ጥያቄ አቀረቡ የተባሉ የወልቃይት ጠገዴ ሰዎችን የሚዘልፉና የሚያንቋሽሹ መልዕክቶችን በገፍ በመርጨቱ ነው። በወልቃይት ጠገዴ የተነሳው የማንነት ጥያቄ ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ መንገድን የተከተለ ቢሆንም ገና ከመጀመሪያው የሕወሓት ባለሥልጣናትን ‹‹ትዕግስታችን አልቋል›› ማስባሉ አስገራሚም አደንጋጭም ነው። የማንንት ጥያቄ መነሳቱን

በመቃወም ልሮች ተካሄዱ እየተባለ ኢቢሲ (ትግርኛ ፕሮግራም) ደጋግሞ የማንነት ጥያቄውን ሲያጣጥልና ማስፈሪያ ሲነዛ እያየን ነው። ሰልፈኞቹ ተናገሩት እየተባለ በቴሌቪዥኑ የሚስተጋባው ነገር አጠያቂ ነው። ትርፍራፊዎች፣ ትምክህተኞች፣ ቅጥረኞች፣ ራስ ወዳዶች ወዘተ ወዘተ. የሚሉ ዘለፋዎች ለኩሩው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ የሚገቡ አይደሉም። የትግርኛው ኢቢሲ ሰልፈኞች ያስተላለፉት ሐሳብ ብሎ ደጋግሞ ለተመልካች የሚጋብዘው ጽሑፍ እንዲህ ይነበባል ‹‹ይመኣዱ ወይ ብበትሪ ወያነ ይመሃሩ›› የዚህ አባባል ግርድፍ ትርጉም ‹‹ይመከሩ ወይም በወያኔ ዱላ ትምህርት ይሰጣቸው›› እንደ ማለት ነው። ማንነትን በመምከር ማስቀየር የሚቻለው እንዴት ነው? የወያኔ ዱላ የተባለውስ ምንድን ነው? ጠመንጃ ይሆን? በወረቀት ላይ የሰፈረ ፊርማ ይዘው ወደ ምክር ቤት በሄዱ ሰዎች ላይ ይህን ያህል ዛቻና ፉከራ ለምን ይስተጋባል?

በቴሌቪዥን ላይ የመታየት ዕድሉ የተሰጣቸው ሰልፈኞች ስለ ራሳቸው ማንነት ራሳቸው እንደሚያውቁት ሁሉ ፊርማ አሰባሳቢዎቹና ፊርማቸውን ያኖሩ ሰዎችም ስለ ማንነታቸው ራሳቸው ያውቃሉ። የማንነት ጥያቄ አንድ ነገር ሲሆን ‹‹ይኽ ለም መሬት›› ብሎ ግዑዙ መሬት የየትኛው ክልል መሆን አለበት ብሎ መሟገት ግን ሌላ ነገር ነው። የ800 ብር ጫማ ማድረግ በቻልንበት ጊዜ ሌላው እንዴት የማንነት ጥያቄ ያነሳል ብሎ የሚቆጩ ሰዎችን ሚዲያ ላይ መቅረቡም ያስገምታልና የዚህ ዓይነቱን አስተያየት ማስተጋባት ተገቢ አይደለም።

የትግራይ መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች ከሚዲያ ሥራ ጥበብ ይልቅ የካድሬነት ሙያን የተካኑ ናቸው። ወደ አንድ ስብስባ ሲጠሩ ከስብሰባው የተገኘን ነገር ለሕዝብ ከማቅረብ ይልቅ ገና ወደ ስብሰባው ሳይሄዱ ምን ዘገባ እንደሚሰሩ ወስነው ጨርሰው ሄደው ፕሮፓጋንዳ የሚሰሩ ናቸው። አንዳንዴም ስለ ስብሰባው የጻፉትን ግጥም ኪሳቸው አውጥተው በስብሰባው ላይ ከማንበብ ጀምሮ ስብሰባውን ለመምራት የሚዳዳቸው ናቸው። በተለያዩ ስብሰባዎች በሕዝብ የሚቀርብ የተለየ ሐሳብን፣ ጥያቄንና እሮሮን በማፈንም ይታወቃሉ። ከገዥው ብድን ፍላጎት ወጣ ያሉ ነገሮች በሙሉ በስብሰባ አዳራሹ ተቀብረው ይቀራሉ። አሁን በወልቃይት ጠገዴው ጉዳይም በዚህ መልኩ ስለሚሠሩ ሁሉንም የአካባቢውን ነዋሪዎች ሐሳብ በሚዛናዊነት ያስተናግዳሉ ብሎ መጠበቅ አይቻልም። የሕወሓት ባለሥልጣናት በጠሩት ሰልፍ ተገኝተዋልና ሕወሓት የሚፈልገውን ነገር ብቻ ማስተጋባቸው አይቀሬ ነው። እነዚህ ሕዝቦች ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ አብረው የኖሩና ለወደፊትም አብረውም የሚኖሩ ናቸውና ጠላትነት ባይዘራ መልካም ነው። ‹‹ሕድሪ መለስ አይኣብርን›› (የመለስን አደራ አንበላም) እየተባለ የሚፎከረው

ለዚህ አካባቢ የታለመው የአቶ መለስ ሕልም ምን ስለሆነ ነው? ለመልሱ ከ24 ዓመታት በፊት በወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ስለተከሰተው ነገር እና ከ40 ዓመታት በፊት በነ አቶ መለስ ደደቢት ውስጥ ስለወጣው የሕወሓት መሪ ፕሮግራም መለስ ብለን ጥቂት ነገሮችን እናስታውስ፡፡

ከ24 ዓመታት በፊት መለስ ብለን በዚያ አካባቢ የነበረን ሁኔታ እንመልከት፡፡ በ1984 ዓ.ም. መጨረሻ ወይም በ1985 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ወደ ሑመራና አካባቢው ጎራ ያለ ሰው ‹‹ትግሬዎች ናችሁ ተባልን›› እያሉ ሲቆጩ ሰዎች ማግኘቱ የተለመደ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ በተደረገው ነገር የሚደሰቱ ሰዎችንም ማየት ይቻል ነበር፡፡ ይህን ቁጭትና ደስታ ያፈራረቀው ሪፈረንደም ተካሂዶ ወይም ሕዝብ ድምጹን እንዲሰጥ ተደርጎ ወልቃይት ጠገዴ ከነ ነዋሪዎቻቸው ወደ ትግራይ ተከለለ መባሉ ነው፡፡ አሁን በዚህ ወቅት በወልቃይትና ጠገዴ አካባቢዎች በመታየት ላይ ያለው የማንነት ጥያቄ እንቅስቃሴና በዚያ አካባቢ ተደረጉ እየተባሉ በቴሌቪዥን በመታየት ላይ ያሉት ሰልፎች የዚያ ከ24 ዓመት በፊት የተከሰተ ነገር ግልባጮችና የዚያን ጊዜውን ሁኔታ የሚያስታውሱ ናቸው፡፡

ባለፉት 24 ዓመታት የወልቃይት ጠገዴን ጨምሮ ከወሎና ከጎንደር የተወሰደ መሬቶችን ጉዳይ እና በዚያ ያሉ የትግራይ ብሔረሰብ አባል ያልሆኑ ሰዎችን መብት የሚመለከቱ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ለአማራ ክልል ባለሥልጣናት እና ለብአዴን/ኢሕዴን ከፍተኛ አመራሮች እየቀረቡ ኖረዋል፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ወደ ትግራይ ሲጠቃለሉ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች መብት ግምት ውስጥ አልገባም ነበር፡፡ በቋንቋቸው የመቀጠምም ሆነ የየትኛው ብሔረሰብ አባል የመሆናቸው ጉዳይ በሕወሓት ተወስኖ ነበር የተሰጣቸው፡፡ ትግሬዎች እንዲሆኑ ተወስኖባቸዋል፡፡

አቶ በረከት ስምዖንን የመሳሰሉ የአማራ ነጻ አውጭ ነን ባዮች ከጎንደርና ከወሎ ተወስዶ ወደ ትግራይ የተጠቃለሉ አካባቢዎችን እና ከመሬቱ ጋር ወደ ትግራይ የተወሰዱ ሰዎችን መብት የሚመለከት ጥያቄ በተደጋጋሚ ሲቀርብላቸው ቦታዎቹ ወደ ትግራይ የተጠቃለሉት በሕዝብ ውሳኔ ነው ሲሉ ይሰሙ ነበር፡፡ ይህ ሕዝብ ውሳኔ እንዴት ተካሄደ? በቀበሌ አዳራሾችና በየዛፉ ሥር እጅ በማውጣት ነው ወይስ የድምጽ መስጫ ካርዶችና ኮረጆዎች ተዘጋጅተው በሚስጢር በተሰጠ ድምጽ? የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓቱ በማን ተዘጋጀ? ማንስ መራው? ታዛቢ የነበሩትስ እነማን ነበሩ? ይህ የሕዝብ ውሳኔ የተባለ አካሄድ ሁሉንም ከጎንደርና ከወሎ የተወሰዱ መሬቶችን በሙሉ የሚመለከት ነበር ወይስ የተወሰኑትን? እነዚህን

መሰል ጥያቄዎች ማብራሪያ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ቢሆንም ጥያቄዎቹን ማንሳቱን አላስፈላጊ የሚያስመስል ታሪካዊ ሐቅም አለ፡፡ ምክንያቱም ነገሮች ሁሉ ገና ድሮ በ1968 ዓ.ም. ደደቢት ውስጥ ተወስነው ያለቀላቸው ናቸውና ነው፡፡

ሕወሓት ገና ከልጅነቱ ወደ ትግራይ ትልልቅ ከተሞች ሰርጎ እየገባ ወይም የተወሰኑ አጥቂዎችን እየላከ ባንክ በማጥቃት ገንዘብ ማግኘት፣ የታሰሩ አባላቱን ማስፈታት እና የመሳሰሉ ሥራዎችን ይሠራ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ተልዕኮ የሕወሓት እግር ከረገጣቸው ከተሞች ውስጥ ሽሬ እንዳስላሴ፣ አክሱም፣ አድዋ፣ መቀሌን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ተልዕኮዎቹ የተሳኩባቸውም ያልተሳኩባቸውም አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ ሕወሓት በትግራይ ትልልቅ ከተሞች ላይ ሙሉ ጦርነት ከፍቶ ድል ቀንቶች ከተሞቹን መቆጣጠር የጀመረው ግን ከመጋቢት 1980 ዓ.ም. ጀምሮ ነው፡፡ በመጋቢትና በሚያዝያ 1980 ዓ.ም. በተካሄዱ ጦርነቶች ከመቀሌና ከማይጨው በስተቀር ሁሉም ይትግራይ ትልልቅ እና ትንንሽ ከተሞች ወደ ሕወሓት ቁጥጥር ገብተው ነበር፡፡ በ1980 ዓ.ም. የክረምት ወር ሕወሓት ከተሞቹን ለቅቆ እንዲሄድ የሚያስገድድ ጥቃት ተሰንዝሮበት ሁሉንም ከተሞች መልሶ ቢያጣም ሕወሓት በ1981 ዓ.ም. ባካሄዳቸው ጦርነቶች ትልልቆቹን ከተሞች ብቻ ሳይሆን መላውን ትግራይ በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል፡፡

በ1980 ዓ.ም. ሕወሓት ከተሞቹን በጦርነት ይቆጣጠር በነበረበት ጊዜ በዚያ የሚገኙትን ነዋሪዎች በተለይም የመንግሥት ሠራተኞችንና ወጣቶች ለ30 ወይም ለ40 ቀናት የሚዘልቅ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ በዚህ የትምህርት ጊዜ የሕወሓት ካድሬዎች በፊት ለፊት ከሚሰጡት ሥልጠና በተጠማሪ በቪዲዮ የተዘጋጀ ትምህርት፣ በሕወሓት ኪነቶች አማካኝነት በዘፈንና በድራማ መልክ የሚተላለፍ መልዕክትም የሥልጠናው አካል እንዲሆን ይደረግ ነበር፡፡ በቪዲዮ ከሚሰጠው ትምህርት ውስጥ ‹‹ትግራይ በሰሜን ከኤርትራ፣ በደቡብ ከኢትዮጵያ፣ በምዕራብ ከሱዳን ጋር የምትዋሰን አገር ናት›› የሚል በካርታ የተደገፈ መልዕክት ይገኝበታል፡፡ ትግራይ በምዕራብ ከሱዳን ጋር የምትዋሰን አገር ናት ከተባለ የወልቃይትና የጠገዴ አካባቢዎች በ1984 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ተካሄደ በሚባለው ሪፈረንደን ወይም የሕዝብ ውሳኔ ሳይሆን ሕወሓት በበረሐ እያለ የትግራይ ግዛት አድርጓቸዋል ማለት ነው፡፡ ትግራይ በደቡብ ከኢትዮጵያ ጋር ትዋሰናለች መባሉ ደግሞ ሕወሓት ከሻዕብያ ጋር ተመሳሳይ የመገንጠል ዓላማን እንዳነገበ መቀጠሉን የሚያሳይ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡

ሕወሓትን ጥለው የወጡ ሰዎች የዚህን አባባል እውነትኛነት በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን መስክረዋል፡፡ ምስክርነታቸው ግልጽ የሚሆነው ‹‹ማንፌስቶ 68›› የተባለውን የሕወሓት ፕሮግራም አስመልክተው ሲናገሩ ነው፡፡ ሕወሓት (ያኔ ተሓሕት ነበር የሚባለው) በተመሠረተ በጥቂት ወራት ውስጥ ‹‹ማንፌስቶ 68›› የተባለው ሰነድ ወጣ፡፡ ከተሓሕት-ሕወሓት መሥራቾች ውስጥ አንዱ የነበሩትና ከድርጅቱ ከተለዩ ወደ 30 ዓመታት ያስቆጠሩት ዶ/ር አረጋዊ በርኸ በግልጽ እንዳሳወቁት ይህ ‹‹ማንፌስቶ 68›› የተባለው የድርጅቱ ፕሮግራም ትግራይን ከኢትዮጵያ መገንጠልን ይሰብካል ብለዋል፡፡ ይህ ማንፌስቶ ትግራይ የኢትዮጵያ ግዛት ሆና እንደማታውቅ፣ ከዳግማዊ አጼ ሚኒልክ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል መደረጓንና ትግል የሚካሄደው ትግራይን መልሶ ነጻ ለማውጣት መሆኑን ይተነትናል፡፡ ዶ/ር አረጋዊ ‹‹ማንፌስቶ 68›› በተለይም ትግራይ ኢትዮጵያዊ አይደለችም መገንጠል አለባት የሚለው ክፍል በሕወሓት ታጋዮች ከፍተኛ ተቃውሞ ስለገጠመው በዝምታ ሻንጣ ውስጥ ተቆልፎበት መቀመጡን ገልጸዋል፡፡ ነገሩ ምቹ ጊዜን እንደመጠበቅ መሆኑንም አልሸሸጉም፡፡

በአሁኑ ጊዜ ‹‹ማንፌስቶ 68›› ተብሎ በተለያዩ ድረ-ገጾች ላይ የሚገኘው ሰነድ የትግራይ ሕዝብ ማለት በትግራይ ውስጥ የሚኖሩትንና በተለያየ ምክንያት ከትግራይ መሬት ውጭ የሚኖሩትን ሕዝቦቿ በሙሉ ያጠቃለለ ነው ይልና በዝርዝር ሲያስቀምጠው ትግርኛ ተናጋሪዎች፣ አፋር፣ አገው፣ ሳሆ፣ ኩናማ፣ ወዘተ. ይላል፡፡ ቀጥሎም የትግራይን መሬት በደቡብ አለውሃ፣ በሰሜን መረብ ሲያካልሉት በምዕራብ በኩል ደግሞ <u>ወልቃይትንና ጸለምትን</u> ያጠቃልላል ይላል፡፡ ጉዳዩ በ1968 ዓ.ም. ላይ ያለቀለት በመሆኑ ነው በ1984 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ውሳኔ ሕዝብ ተካሄደ መባሉን የይስሙላና ይህን አስመልክቶ ጥያቄ ማንሳቱን ጊዜ ማባከን የሚያደርገው፡፡

ይህን ማንፌስቶ በጽሞና ለሚመለከተው ‹‹የትግራይ ሕዝብ›› እና ‹‹የትግራይ መሬት›› የሚለውን በሚያምታታ መንገድ ነው ያስቀመጠው፡፡ በለተያየ ምክንያት ከትግራይ ውጭ ያሉት የትግራይ ሰዎች ወደ ትግራይ ምድር ይመለሳሉ የሚል ይመስልና ከትግራይ ውጭ ያሉት የትግራይ ሰዎች የሚኖሩበት መሬት የትግራይ መሬት ይሆናል በማለት እርምጃ ለመውሰድ ያለውን ዝግጁነት ያሳያል፡፡ የወልቃይትንና የጸለምትን ሰዎች የትግራይ ሰዎች ናቸው የሚለው ምኞት ሲተገበር መሬቱ ወደ ትግራይ መጠቃለሉ በተግባር ታይቷል፡፡ ይህ አተገባበር ደግሞ ‹‹በተለያዩ ምክንያቶች ከትግራይ ውጭ የሚኖሩ›› ከሚባሉት ሰዎች ይልቅ እነሱ ስለሚኖሩበት መሬት የመጨነቅና የመጠበብ ዝንባሌን የሚያሳይ ነው፡፡

ታላቋን ትግራይ መመሥረቻ ፕሮግራም ተብሎ በጥቂት ግለሰቦች ተጽፎ ብዙው የሕወሓት አባል ስለተቃወመው ሻንጣ ውስጥ የተቆለፈበት ‹‹ማንፌስቶ 68›› በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በኤርትራ በኩል በሰፊው መነጋገሪያ ሆኖ ነበረ። የሕወሓቱ ማንፌስቶ ከትግራይ ውጭ ያሉት ትግርኛ ተናጋሪዎች፣ አፋሮች፣ ኩናማዎች፣ ሳሆዎች ወዘተ. ከያዙት መሬት ጋር የትግራይ ናቸው ስለሚል መንገዱ አልጋ በአልጋ ከሆነ ኤርትራ ውስጥ ያሉት ትግርኛ ተናጋሪዎች ከነ መሬቱ (ሰራየ፣ አካለጉዛይ፣ ሃማሴን) ወደ ትግራይ ይካተታሉ። እነዚህ ከትግራይ ውጭ ያሉና ትግሬዎች ናችሁ የተባሉ ሰዎች በዚህ አተረጓጎም ካልተስማሙ ጠላት ተደርገው የመታየት አደጋ ያንዣበበባቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ‹‹መሬትን እና ሕዝብን›› ቀላቅሎ የተቀመጠ ፕሮግራም ‹‹ከትግራይ ውጭ ያሉ አፋሮች›› ሲል የኤርትራ አፋሮች ያሉበትን ምድር ወደ ትግራይ ለማጠቃለል የቋመጠ መሰሪ አባባል ነው የሚል ስጋት የፈጠረውና በቡሬ ግንባር ጦርነት ሲከፈት ይህ ምኞት ተግባራዊ ሊሆን ነው የተባለው ለዚህ ነው።

በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ውዝግብ አልነበረበትም በሚባለው በቡሬ ግንባር ጦርነት ሲከፈት ‹‹የማንፌስቶ 68›› ሁለተኛ ደረጃ ካርታ ሊወለድ የተቃረበ መስሎ የነበረ መሆኑን የሕዝባዊ ግንባር ኦፊሻል ድረ-ገጽ ‹‹ሻባይት ዶት ኮም›› ባተስተጋባው ጩኸትም መረዳት ይቻላል። በዚህ ድረ-ገጽ አባባል ያኔ አሰብን ጨምሮ በኤርትራ ምድር የሚገኘው የአፋሮች ምድር ወደ ታላቋ ትግራይ የሚገባበት ጊዜ የተቃረበ መስሎ ነበር።

ይህን የመሰለ ትኩሳት የሚፈጥረው የሕወሓት የተደበቀ ወይም በይፋ ያልተሻረ ፕሮግራም መኖር ብቻ ሳይሆን ሕወሓት ከ40 ዓመታት በፊት የወጣውን ‹‹የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ነኝ›› የሚል ስሙን ሳይቀይር መቀጠሉ ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ድርጅቱ ምን ዓይነት ነጻነትን ይጠብቃል ብሎ ለመጠቀየቅ የሚገፋፋ ነው። የመቀሌው የሰማዕታት ሐውልት 51 ሜትር ርዝመት ያለው ነው። የ51 ሜትር ርዝመቱ ትርጉም ምን መሆኑ ሲገለጽ ‹‹የመጀመሪያው ምዕራፍ በማለፊያ ውጤት (51 ከ100) በማግት መጠናቀቁንና ሁለተኛው ምዕራፍ የሚጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው›› ይባላል። ቁመቱ 50 ሜትር ከመሆን ይልቅ 51 የሆነው ቀጣት ስራ መኖሩንና 51፣ 52፣ 53 … እያለ 100 እስኪደርስ ይቀጥላል ለማለት መሆኑ በይፋ እየተነገረ ነው።

ትግራይን ራሷን የቻለች ትልቅ አገር አድርጎ ለመመሥረትና ለማኖር ሲል ሕወሓት ‹‹የኢትዮጵያን ባልካናይዜሽን›› ሆነ ብሎ እውን ያደርጋል የሚል ስጋት ይስተጋባል፡፡ አደገኛው የዘር ፖለቲካ ኢትዮጵያ ውስጥ የተተገበረውና ሕዝቦች እንዲናቆሩ የሚደረገው የዚህ የዘር ፖለቲካ ዶ/ር አረጋዊ ‹‹… 1987 ዓ.ም. ላይ የወጣው ሕገ መንግሥት (አንቀጽ 39:1) የሕወሓትን አመራር የረዥም ጊዜ ዝንባሌ የሚያሳይ ነው…›› ካሉ በኋላ የሕወሓት መሪዎች አሁን ያላቸው ገጽታ በውስጣቸው ካለው ድብቅ ዓላማ እና ከአካሄዳቸው ጋር እየተጋጨ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ‹‹…አመራሩ ያጠለቀው የተራማጅነት ማስክ ብዙዎችን ተመራማሪዎችን ጨምሮ ግራ ሲያጋባ የሚታየው ለዚህ ነው…›› ብለዋል፡፡



# የወልቃይት ሕዝብ ጥያቄና የትግራይ ‹‹ጋዜጠኞች››

አቶ ግዛቸው አበበ

ሕወሓት ገና ሲመሠረት ትግራይንና ኤርትራን ጨምሮ ሌላውን የኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ከመቶ ዓመታት በፊት አማራ በቅኝ ግዛትነት ይዞ የኢትዮጵያ ክፍል አድርጓቸዋል ሲል ይሰብካል፡፡ ሕወሓት ይህን መሰል የፈጠራ ታሪክ የሚያወራው አንደኛ ሕዝቦችን በማጋጨት የራሱን ትግል ለማቅለል፣ ሁለተኛ ትግራይንና ኤርትራን የመገንጠሉን ሒደት በቀላሉ ለማሳካት፣ ሦስተኛ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች እርስ በርሳቸው እንዲናቆሩና ለኢትዮጵያ ብሎ የሚቆም ሕዝብ እንዳይኖር ለማድረግ አራተኛ የዘመነ መሳፍንቱን አገር የመበታተን እኩይ ዘመቻ ያከሸፉትን ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የመሰለ የአንድነት ጥመኛ ከተነሳ እሱን የሚከተል ሕዝብ እንዳይኖርና የዚህን የዘመነ ግንባሩን አገር የማፈራረስ ዘመቻ እንዳያደናቅፍ በማሰብ ነው፡፡

ሕወሓት ከፊት ለፊቱ አንድ አደጋ ሲጋረጥ ፈጥኖ ሕዝቦችን የሚያጋጭ ነገር እንዲከሰት በማድርግ ራሱን ለማዳን ጥረት የሚያደርግ መሆኑ በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ምርጫ 1997ን ተከትሎ አዲስ አበባ ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የጥቃት ዒላማ የተደረጉ የሚያስመስል ዜናዎችን ከመሥራት ጀምሮ ‹‹እቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ›› የሚል ዘመቻ የመጀመር ፍንጭ የታየ የሚያስመስሉ ፕሮፓጋንዳዎችን በመንዛት ሕዝቦች እንዲቃቃሩ ለማድርግ ሞክሯል፡፡

ምርጫ 1997ን ተከትሎ የሕወሓት ካድሬ ወጣቶች መቀሌ ከተማ ውስጥ የትግራይ ሕዝብ ሌላው ኢትዮጵያዊ በጠላትነት የተነሳበት የሚያስመስል ቅስቀሳ ማድረጉም አይዘነጋም፡፡ የምርጫው ውጤት እንደታወቀ የሕወሓት ካድሬ ወጣቶች ድምጽ ማጉያ በተሸከመ መኪና መቀሌ ከተማን እየዞሩ ነፍጠኞች ተነሱብህ! ትምክህተኞች ተነሱብህ! እያሉ በመቀስቀስ ሕወሓት ሥልጣን ካጣ የትግራይ ሕዝብ በሰላም መኖር የማይችል የሚያስመስል የስጋት ጭጋግ ለመፍጠር ሲሞክሩ ነበር፡፡ የዚህ ዓይነት ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ከ1997 ዓ.ም. በኋላ በዘዴ እየተሠራ መቀጠሉ በተለያዩ መንገዶች የሚታይ ነው፡፡

ለትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲን ጠብ ማድርግ ያልቻለው፣ ራሱን በደርግ ቦታ ተክቶ የደርግን የሥልጣን ጥማት ተጋርቶ ከኔ ሌላ ትግራይን መግዛት የሚገባው የለም ያለው ሕወሓት ለራሱ ህልውናና ለአውራዎቹ ምቾት ሲባል የትግራይን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አይጥና ድመት ሊያደርገው መሞከሩ ከራሱ ከትግራይ ሕዝብም የተሰወረ አይደለምና የትግራይ ሕዝብ አታጋይና አማራጭ የሚሆነው የፖለቲካ ፓርቲን ሲያልም ኖሯል፡፡

የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ትግራይ ገብተው ቅስቀሳ ሲያደርጉና ስብሰባ ሲያካሂዱ ሕወሓት ካድሬዎቹን ወደ ቦታው በመላክ ዱላ ቀረሽ የስድብ ናዳ እንዲያወርዱ በማድረግ፣ ስብሰባዎች በንትርክ የተሞሉና ቁም ነገርም የማይደመጥባቸው እንዲሆኑ ጠንክሮ በመሥራት፣ ወደ ስብሰባዎች የሔዱ ሰዎችን በማስፈራራት እና በመሳሰሉት መንገዶች መሰናክል ይፈጥራል፡፡ ሕወሓት በስብሰባዎች ላይ የተነገሩ ሐሳቦችን ቆንጽሎና አጣምሞ በመውሰድ የትግራይ ሕዝብ ተሰደበ የሚል ውንጀላም ይሰነዝራል፡፡

በቀድሞ የሕወሓት አባላት አማካኝነት የተመሠረተው አረና የተሰኘው ፓርቲ ለሕወሓት እንደ ትልቅ ስጋት ተደርጎ ይታያል፡፡ የዚህ ፓርቲ አባላት የሆኑ የትግራይ ሰዎች በገጠርም በከተማም ለከፍተኛ ችግር ይዳረጋሉ፡፡ ኑሯቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ከሚያናጋ ከፍተኛ እርምጃ ከመውሰድ ጀምሮ በጎረቤት እንዲገለሉ እስከ ሚያደርግ ተራ የማቃቃር ሴረም ይሸረባል፡፡

ሕወሓት ለራሱ ህልውናና ለባለሥልጣናቱ የምቾት ኑሮ ቀጣይነት ሲል የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በጥርጣሬ እንዲተያይ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ ሌሎች ሕዝቦች የትግራይን ሕዝብ በጠላትነት እንዲያዩት በማድርግም ክፍፍሉ የመረረ እንዲሆን ለማድርግ ይሠራል፡፡ በዚህ መዘን ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች የትግራይን ሕዝብ በጅምላ የሚያጥላላ ጽሑፍ ሲያስነብቡና ንግግርም ሰያደርጉ ይሰማሉ፡፡ ይህን መሰሉ አሳፋሪና አሳዛኝ ሥራ የትግራይና የኤርትራ ሕዝቦች ለኢትዮጵያ አንድነት ነቀርሳዎች ናቸው ከሚሉ ነገር ግን ራሳቸው ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን አክብረው በመያዙ ላይና ወገኖቻቸውን በማክበር ረገድ ችግር ካለባቸው በስደት በውጭ አገር ከሚኖሩ ሰዎችና ቡድኖች የመነጨ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

የትግራይን ሕዝብ በጅምላ ‹‹ወያኔ›› ብለው ከሚጠሩት ጀምሮ ይህን ሕዝብ ኮካኮላ፣ ፍልስጥኤም ወዘተ. እያሉ በጅምላ የሚሸረድዱት ሰዎችና ቡድኖች ሳይታወቃቸውም ሆነ አውቀውት እንደ ሕወሓትና ኦነግ ያሉትን ጠባብ ቡድኖችን አጀንዳ እያራመዱ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል፡፡ እነዚህ ጠባብ ቡድኖች በአንድ በኩል እንወክለዋለን የሚሉት ሕዝብ ሌላውን ኢትዮጰያዊ እንዲጠራጠርና በጠላትነት እንዲያይ የሚሠሩ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ሕዝብ እነሱ እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ እንዲጠራጠርና በጠላትነት እንዲያይ ይሠራሉ:: በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብን ቀርቶ ለአንድ የእግር ኳስ ቡድን ተሰልፈው የተጫዎቱ ዐሥራ አንዱን የአንድ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች በአንድነት ፊርጆ መላ ማንነታቸውን መተንተን ለስህተት የሚዳርግ ጭፍን አካሄድ መሆኑ የሚታበል አይደለምና ኦሮሞው ሁሉ፣ ትግሬው ሁሉ፣ አማራው ሁሉ፣ ሐበሻው ሁሉ ወዘተ. እያሉ የፍረጃ ወሬ የሚያወሩ ተቃዋሚዎች፣ የሚዲያ ሰዎች፣ የገዥው ቡድን ባለሥልጣናትና ካድሬዎች በአንድ መስመር ለጥፋት እየተሰለፉ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል::

የትግራይ ሕዝብ በአንድ በኩል ከሌላው ሕዝብ ያላነሰ ችግር ውስጥ እየገባ ያለ ሕዝብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ያላነሰ የኢትዮጵያዊነት ፍቅር የሚቃጠል ሕዝብ መሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡ ይህን ሐቅ አለማወቅና አስተሳሰብን ከሐቁ አንጻር አለመግራት ለትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በጠላትነት ከመሰለፍ የማይተናነስ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ ትግልም ሆነ መማማር ብልሃትንና ታጋሽነትን እንጂ ጠላትነትንና ስሜታዊነትን አይሹም፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ያጡት እንዲህ ዓይነት ጥበብና ትዕግስት ያለው የተቃዋሚ መሪ ነው፡፡ አንዳንድ በዕድሜ የገፉም ሆኑ ጎልማሳ የሕወሓት አውራ ሰዎች አማራውን፣ ኦሮሞውንና ሌላውን ሕዝብን የሚያጥላላ ነገር ስለሚናገሩ ለዚህ መልስ የሚሆነው የትግራይን ሕዝብ ማጥላላትና ማንቋሸሽ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች በትክክለኛው የኢትዮጵያዊነት ትግል ጎዳና ላይ አለመሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡

በትግራይ ሕዝብ ላይ ጥርጣሬና ጥላቻ የሚነዙ ሰዎች የሕወሓትን ባለሥልጣናትን ድርጊት በማየት፣ በየአካባቢያቸው ያሉ አዳዲስ ባለጸጋዎች ሆነው በማቆጥቆጥ ላይ ያሉ የትግራይ ሰዎችን በመቁጠር፣ በገዥው ቡድን ሚዲያ ላይ የሚስተጋቡ መሰሪ ቅስቀሳዎችን ያለ ጥንቃቄ በመጋትና ከመሳሰሉት ትዝብቶቻቸው በመነሳት ኢትዮጵያ ውስጥ የደቡብ አፍሪካውን የመሰለ አንዱን ሕዝብ በጅምላ አቅፎ እየጠቀመ ሌሎችን ሕዝቦች እያገለለና እየዘረፈ

የሚያራቁት ወያኔያዊ ሥርዓት የሰፈነ ሆኖ ይሰማቸው ዘነድ ራሳቸውን ያዘናጉ ሰዎች ናቸው። ይኽ ደግሞ ከማንም ይልቅ ለጸረ አንድነቶችና ለኢትዮጵያ ጠላቶች የሚጠቅም ነው። አንድን ሕዝብ በጅምላ የሚጠሉና የሚዘልፉ ሰዎች በዚህም ሆነ በዚያ የሕወሓትን ሕዝቦችን የማናቆር አጀንዳ እያራመዱ መሆኑ ሊያውቁት ይገባል።

የወያኔ ተቃዋሚዎች ነን የሚሉ ብዙ የፖለቲካና የሚዲያ ሰዎች አደገኛ መንገድ እየተከተሉ መሆኑን በ2008 ዓ.ም. በዚህች አገር ውስጥ እየተከሰቱ ያሉትን ግጭቶች ተከትሎ የያዙት አቋምና የሚናገሩት ነገር ያጋልጣቸዋል። በየአካባቢው ተቀሰቀሱት አመጾች በሕወሓት የተሳሳተ አካሄድና አደገኛ አንቀጾችን በያዘው ሕገ መንግሥት ምክንያት የተፈጠሩ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የሚያጋጩ፣ በአገሪቱ አንድነት ላይ አደጋ የጋረጡ፣ ወደፊት ሊመጣ የሚችልን አስከፊ አደጋን የሚያሳክቱ ቢሆንም አመጾቹን (ተቃዋሚዎቹን) በኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ሥር ወደ አንድ በማምጣት በገዥው ቡድን ላይ እንዲያነጣጥሩ ማድርግ ሳይችሉ ቀርተዋል። አመጾቹን ጠለቅ ብለው አይተው በችግሩ ዋና መንስኤ ላይ ሳይሆን በችግሩ ጥቃቅን ምልክቶች ላይ አተኩረው ይታያሉ። ተቃውሞዎች ሁሉ ወደ ሥልጣን ያመራሉ በሚል ችኩል አስተሳሰብ አመጾቹ ሰርግና ምላሽ ሆነውላቸው ይታያሉ። ይህ መውረግረግ ጊዜው ስላልደረሰ እንጂ ከማንም ይልቅ ለግንጠላ ቡድኖች የተመቸ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን ያስከተለው የሚዲያዎችን፣ የካድሬዎችንና የባለሥልጣናትን የማንአለብኝነት እንቅስቃሴዎች ጥበበኛ ባልሆነ መንገድ በጭፍን የመቃወም አባዜ ነው።

ወደ ትግራይ መገናኛ ብዙሃን ካድሬዎች ስንመለስ፣ የትግራይ መገናኛ ብዙሃን የሕወሓት የፖለቲካ ካድሬዎች፣ በሕወሓት ጥላ ሥር የተኮለኮሉ የተለያዩ ማኅበራት ያሰለፏቸው ካድሬዎች ወዘተ. ለማንም የማይተኙ የታዘዙትን ነገር ሁሉ ከትዕዛዙ በላይ ርቀው በመሄድ ለመፈጸም የተዘጋጁ ናቸው። ትዕዛዙ ከላይ እስመጣ ድረስ ለምን? እንዴት? ብለው የማይጠይቁ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች እንደ አቶ ስዬ አብርሃም፣ አቶ ገብሩ አሥራት፣ ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ ወዘተ. ያሉ የቀድሞ የሕወሓት ትልልቅ ሰዎች ሲዘልፉና ሲያብጠለጥሉ እንኳን ትንሽ ቅር የሚላቸው አይደሉም። እሾህ-አሜኬላ (አቃቅማ)፣ ተላላኪ፣ ቅጥረኛ ወዘተ. ከሚሉት ዘለፋዎች ጀምሮ ለመድገም አሳፋሪ የሆኑ ስድቦችን ያለ ምንም ይሉኝታ አውርደውባቸዋል። እነዚህ የሕወሓት ካድሬዎችና የሚዲያ ሰዎች ባለ ተራ ሆኖ ለተገኘው የሕወሓት አውራ የሚመለሱ አይደሉም። አንድ ወይም ሁለቱ የሕወሓት አውራዎች ከጉጅሌው ወጣ ካሉ ይኸው ዘለፋና ስድብ ይጠብቃቸዋል። አቶ ዓባይ ወልዱም ይሁን ጌታቸው ረዳ

ከሕወሓት ጥርናፌ ወጣ ካሉ ይኸው ዘለፋና ስድብ እንደሚጠብቃቸው ያውቁታል። ከልጅ እግሮቹ ጀምሮ ዕድሜ እስከጠገቡት የሕወሓት ካድሬዎች በዚህ በጭፍን የመነዳትና ልዩነቶችን የጠላትነት ምንጮች አድርጎ በማየት አባዜ የሰከሩ ሆነው የተቀረጹ ሰዎቸ ናቸው።

በዚህ ወቅት የትግራይ መገናኛ ብዙሃን ካድሬዎችና ባለሥልጣናት በወልቃይት ሕዝብ ላይ ይህን የተለመደ ባሕርያቸውን በማንጸባረቅ ላይ ናቸው። ተካሄዱ የሚባሉ ሰልፎችን፣ ስብሰባዎችንና የሕዝብ አስተያየት የተሰበሰበባቸው ቃለ ምልልሶችን ተከትሎ በመስተጋባት ላይ ያለውን ማስፈራራት፣ ዘለፋ እና ትችት የካድሬዎችና የባለሥልጣናት ድምጽ እንጂ የትግራይ ሕዝብ ድምጽ አድርጎ መውሰድ ለስህተት ሊዳርግ ይችላል። የሚሰማው ድምጽ ሁሉ ከአንድ ጭንቅላት የወጣ እስኪመስል ተመሳሳይ ድምጽ የመሰለው ለዚህ ነው። እውነተኛ የሕዝብ ድምጽ ከሆነ የተለያየ አስተያየት መደመጥ ነበረበት። ድምጹ የሚሰማለት ሰው ሁሉ የማንነት ጥያቄ አቀረቡ የተባሉ ሰዎችን ትርፍራፊዎች፣ ምቀኞች ወዘተ. እያለ ከመዝለፍ ጀምሮ እርምጃ ይወሰድባቸው፤ ለፍርድ ይቅረቡ ወዘተ. እያለ ተመሳሳይ የጥላቻ ቃላት መናገር የሚችለው በጥርናፌ ውስጥ ገብቶ መመሪያ ተቀብሎ ሲናገር ብቻ ነው። ይኸ ደግሞ የኢቢሲ ጋዜጠኞች በዓመት በዓል ዋዜማዎች ወደ ገበያ ወርደው የዶሮና የሽንኩርት ዋጋ ጥሩ ነው፤ ርካሽ ነው፤ ከአምናው ጭማሪ አላሳየም ወዘተ. የሚሉ ሰዎችን ብቻ መርጠው ቴሌቪዥን ላይ እንደሚቀርቡት ዓይነት አሠራር ነው። ዶሮ 200 እና 185 ብር ሲሸጥ ርካሽ ነው ማለት የሚችሉት እነማን መሆናቸው የታወቀ ነው።

ትግራይ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ በስብሰባዎች ላይ ተናገሩ ተብለው በሚዲያ ላይ የሚቀርቡ ሰዎችና በአጋጣሚ ጎዳና ላይ ከተገኙ ሰዎች ጋር የተደረጉ መስለው የሚቀርቡ ቃለ ምልልሶች ብዙውን ጊዜ ቅድም ዝግጅት ተደርጎባቸው ከተመረጡ ሰዎችና ቡድኖች ጋር ጨዋታዎች መሆናቸው የታወቀ ነው። በዚህ ዓይነት የመጠርነፍ አሠራርና በጉጅሌ ተደራጅቶ የመሥራት ሒደት በለባቸው ስብሰባዎች ላይ ለየት ያለ ነገር መናገር ከካድሬዎችና ከባለሥልጣናቱ ግልምጫንና እርግጫን የሚያስከትል ቢሆንም ከተመክሮዎች ከመነሳት ትክክለኛውንና ተገቢውን ነገር የሚናገሩ ሰዎች ሰዎች ይታጣሉ ማለት አይቻልም። ነገር ግን ወደ ሚዲያዎች የሚቀርበው በካድሬዎች የተመረጠው ወይም የሚዲያ ሰዎች ከአለቆቻቸው የልብ ትርታ ጋር ይስማማል ብለው የመረጡትን ብቻ ነው።

ለዚህ ነው በትግርኛው ቴሌቪዥን ትግሬ አይደለንም ያሉ ሰዎች እንደ ወንጀለኞች ተደርገው ሲብጠለጠሉ ብቻ የሚሰማው፡፡ አማራ መሆናችንን የፌደሬሽን ምክር ቤት ያስከብርልን ብለው ጥያቄ ያቀረቡ ሰዎች ልማት የሚያደናቅፉ፣ በአገርና በሕዝብ ላይ ጠላትነት ያራገቡ ተደርግው ይገለጻሉ፡፡ ለፍርድ ይቅረቡ ይባላሉ፡፡ በአንዳንዶች ዘንድ ደግሞ በወያኔ በትር እርምጃ ይወሰድባቸው ይባላሉ፡፡

የወልቃይት ሕዝብ ሕወሓት ለሥልጣን በቅቶ አካባቢውን ወደ ትግራይ ካጠቃለለበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ሕወሓት በበረሃ እያለም የጥቃት ዒላማ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የወልቃይት፣ ጸገዴ፣ ጠለምትና የአካባቢዎቹ ሕዝብ ገና ከድሮው የሕወሓት አያያዝ ስላላማረው ጠመንጃ እስከ ማንሳት የደረሰባቸው ጊዜያት በርካቶች ናቸው፡፡ ከ1983 ዓ.ም. በፊት ባሉት ጊዜያት ከኢዲዩ እና ከኢሕአፓ ጋር ወግነው የሕወሓትን የመሬት ነጠቃ እርምጃ ለማቆም ሞክረዋል፡፡ ከ1983 ዓ.ም. በኋላም እንዲሁ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል፡ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በአካባቢው የትጥቅ ትግል ሲያደርግ የነበረው ‹‹ከፋኝ›› የተባለ ቡድን በአብዛኛው የዚህን አካባቢ ሰዎች ያቀፈ ነበር፡፡ የዚህ ቡድን አባል የነበሩና በአሁኑ ወቅት በስደት አውስትራሊያ ውስጥ ከሚገኙት በርካታ የከፋኝ አባላት አንዱ የሆኑት አቶ አዘዘው የተባሉ ሰው የከፋኝን ትግል ሲገልጹት እንዲህ ይላሉ ‹‹…ደርግ ወደቀ በኋላ አገራችን በተራና አላዋቂዎች ሰዎች እንዲሁም ኃላፊነት በጎደላቸው ሰዎች መመራት መጀመሯን ስናይ እነዚህን በዘር የሚሸነሽኗትን የታሪክ ደንቆሮዎች ልንዋጋ ወጣን…››

የወልቃይት ሕዝብ ያዋጣኛል ያለው ነፍጥ አንግቦ ሕወሓትን ሲፋለም ሌላው ደግሞ በገፍ ወደ ሱዳን ተሰድዷል፡፡ ከስደተኞቹ ውስጥ አብዛኞቹ በዕድሜ የገፉት የወልቃይት፣ ጸገዴና ጠለምት አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ሱዳን ውስጥ ሰፍረው በዚያው ኑሯቸውን በግብርና ሥራ እየገፉ በርካታ ዓመታት አሳልፈዋል፡፡ የነዚህ ስደተኞች ቁጥር ወደ 22ሺህ የደረሰበት ወቅት ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች በስደት ሱዳን ውስጥ ቢኖሩም ከፋኝ በሚል ቡድን ሥር ተሰልፈው የሚዋጉ ወገኖቻቸውን አልረሷቸውም፡፡ የሕወሓት ወዳጅ በሆነው የሱዳን መንግሥት መሬት ላይ ተቀምጠው ከፋኝን በግልጽ መርዳት ባይችሉም ‹‹ሰንዲቅ በሪድ›› የሚል ስም ተደራጅተው ገንዘብ እያዋጡ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና ቁሳቁስና ሌላም አስፈላጊ ነገር እየገዙ በመላክ አጋርነታቸውን አሳይተዋል፡፡

በ1985 ዓ.ም. የሱዳን መንግሥትና ሕወሓት በተጣሉበት ወቅት በዚያ የሚኖሩ ታቃዋሚዎችን የሚያበረታታ ነገር ተጀምሮ ነበር። ሕወሓትን የሚቃዎሙ ቡድኖች በግልጽ ጽሕፈት ቤት መክፈትና መደራጀት ችለው ነበር። ይህ አጋጣሚ ለከፋኝም ጥሩ ዘመንን ፈጥሮለት የከፋኝ እንቅስቃሴ ተጧጡፎ ነበር። በዚህ ስጋት የገባው ሕወሓት ተሯሩጦ ከሱዳን መንግሥት ጋር ሲታረቅ ግን ነገሮች ሁሉ ለከፋኝ ጨለማ ሆኑበት። የከፋኝ ደጋፊዎችን ከወያኔ ጋር ታረቁ ብሎ በማግባባት ለማዘናጋት ከመሞከር በየሰበቡ እየወነጀለ ማሰርና ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱን ተያያዘው። እርምጃው ከፋኝን የኋላ ደጋፊ ደጀን ብቻ ሳይሆን ከፋኝን ራሱን መረጋጊያ ቦታ፣ ማፈግፈጊያ መሬትና የቆሰሉ ታጋዮቹን መንከባከቢያ ቦታ አሳጥቶታል።

ከፋኝ የተባለው የውጊያ ቡድን እየከሰመ ሲመጣ አባላቱ ቀድመዋቸው የተሰደዱትን ሰዎች ለመቀላቀልና ወደ ሱዳን በስደተኛነት ለመግባት ተገደዱ። በዚህ የስደት ቦታ ለረዥም ጊዜ ከተቀመጡ በኋላ ብዙዎቹን የአውስትራሊያ መንግሥትና ሌሎችም አገራት ወደ ምድራቸው እንዲገቡ ፈቅደውላቸው በአሁኑ ጊዜ በብዙ አገራት ተበታትነው ይኖራሉ። እነዚህ ስደተኞች ሕወሓት ታሪክ አዋቂዎችንና በዕድሜ የገፉ በዘዴ እያጠፋ ነው ሲሉና ወደ ስደት እንዲሄዱ አድርጓል ሲሉ ይወነጅላሉ።

# ወልቃይት፣ ጠገዴ እና ጠለምት

## በዓይኔ ካየሁትና ከታዘብኩት

አቶ ያሬድ ጥበቡ

### መግቢያ

የዛሬ 39 ዓመት ግድም ለሦስት ዓመታት ያህል ከሰኔ 1969 እስከ ሰኔ 1972 ዓ.ም. ድረስ በጠለምት፣ ዋልድባ፣ ቆላወገራና ወልቃይት ውስጥ የኢሕአፓ ሠራዊት አባል በመሆን በእግሬ ተጉዣለሁ። በአማካይ በቀን 5 ሰዓት እንጓዝ ስለነበር፣ በዓመት 9000 ኪሎ ሜትር፣ በሦስቱ ዓመት ቆይታዬ 27000 ኪሎ ሜትር ያህል መንገድ ተጉዣለሁ ማለት ነው። ዛሬ እነዚህ አካባቢዎች በነዋሪው ሕዝብና በአገዛዙ መሃል የማንነት ጥያቄ የውጥረት ማዕከል ሆነዋል። ከ39 ዓመታት በፊት ወልቃይትንና ጠለምትን ሳውቃቸው ምን ይመስሉ እንደነበር የማስታውሰውን ያህል ባካፍልስ ብዬ ብዕሬን አነሳሁ።

የምሰጠው ምስክርነትና የማነሳው ክርክር በማውቀው የመልክዓምድር አቀማመጥና የሕዝቡ ባህል ላይ የተመሠረተ ነው። የክርክሬ ማጠንጠኛ፣ እንደ ተከዜ ዓይነት ታላላቅ የተፈጥሮ ወሰኖች በትናንሽ አይዲዮሎጂዎች ቢገሰሱ ከፍተኛ ውዝግብና አለመረጋጋትን ስለሚያስከትሉ ጥንቃቄን ይሻሉ የሚል ነው።

በተጨማሪም የተከዜን ዓይነት የተፈጥሮ ወሰኖች ተሻግረው ከአጎራባች ሕዝብ እቅፍ ውስጥ የተስተናገዱ ማኅበረሰቦች፣ ያስጠጋቸውን ሕዝብ ማንነት የመፈታተን መብት ሊኖራቸው አይገባም ብዬም ለመከራከርም ነው። ተከዜ፣ ታላቁ የተፈጥሮ ወሰን ወሎና ጎንደርን አያዋስነ ተከዜን ከሚቀላቀለው የጽላሬ (ጥራሪ) ወንዝ ጀምሮ፣ ትግራይንና ወሎን፣ ትግራይንና ጎንደርን፣ ከዚያም ጎንደርንና ኤርትራን የሚያዋስነውን ታላቁን የተከዜ ወንዝ፣ ከምንጩ ከኩል መስክ ተነስቶ ሱዳን ከሰላ አካባቢ እስኪገባና አትባራ ተብሎ እስኪሰየም፣ በነዚህ በተጠቀሱት የክፍላተ አገራት ወሰኖች ሁሉ በእግሬ ያቆራረጥኩና በሁለቱ አይኖቼ ያየሁ ሰው በመሆኔ፣ ስለ ድንበር አካለዩ ተከዜ መናገር ከሚችሉ ጥቂት ኢትዮጵያውያን መሃል ነኝ።

በመጀመሪያ ተከዜን ያየሁት በሰኔ 1969 ዓ.ም. ኃይል 17 የምትባል የኢሕአፓ ሠራዊት አባል ሆኜ፣ ከአሲምባ ትግራይ ተነስተን ወደ ጠለምት ጎንደር ባደረግነው ጉዞ ወቅት ነው። የግባን ወንዝስንሻገር የኮንጎ ላስቲክ ጫማዬን የሰኔ ውኃ ሙላት ይዞት ሄዶ ስለነበር፣ በጨርቅ በተጠቀለለ እግር እየተንዠኩ ነው ተከዜን የተሻገርኩት። ወደጠለምት መሻገሪያው በጣም ረበዳ ሸለቆ ስለነበር፣ የተከዜን ገመገም ጠዋት መውረድ የጀመርን፣ ወንዙን ተሻግረን አቀበቱን እስክንወጣ ቢያንስ የስድስት ሰዓት መንገድ እንደወሰደብን ትዝ ይለኛል። እጅግ አድካሚ ጉዞ ነበር። ከሰዓት በኋላ ጠለምት ውስጥ ከሚገኝ መንደር ደረስን። ከፀሐይ መግቢያ አቅጣጫ ታላቁ የአቤር ተራራ ቁልቁል በንቀት ይመለከተንም፣ ያስፈራም እንደነበር ትዝ ይለኛል። ቁልቁል ወደመጣንበት የተከዜ ሸለቆ የሚገፈትረን ነበር የሚመስለው። ልክ እንደኛ ሁሉ አስቸጋሪውን የተከዜ ሸለቆ አቋርጠው የመጡ የትግራይሰዎች ከነባሩ የስሜን ሰው ጋር የጠለምትን ማኅበረሰብ መሥርተው፣ ትግርኛም አማርኛም እየተናገሩ ይኖራሉ። ከአዴት፣ ከአቢይ አዲ፣ ከአክሱም አካባቢ ከጉማ አምልጠው ወይም የሰው ሕይወት አጥፍተው፣ ወይም ችግር አብሮአቸው ጠለምት ላይ ከወባና ወበቅ ጋር እየታገሉ፣ የተከዜን ገመገም ይዘው የሰፈሩ የትግራይ ሰዎች ብዙ ናቸው። ጎንደር መሬት ላይ የሰፈሩ ትግራዋዮች።

አሲምባ የነበረው የኢሕአፓ ሠራዊት በየካቲት 1970 ዓ.ም. ‹‹ትግራይ ለትግሬዎች›› በሚል በሕወሓት ድንገት ያልታሰበ ጥቃት ተሰንዝሮበት በብዙ መቶ ለሚቆጠሩ ጓዶች ሞትና መቁሰል ምክንያት ሆነ። ትግራይ ውስጥ መቆየት ስላልተቻለም ወደ ኤርትራ ማፈግፈግ የግድ ሆነ። ሠራዊቱ በጀብሃ አስጠላይነት ሥር ስድስት ወራት ተኮምቢያ አካባቢ፣ ጋሽ ወንዝ ዳር ከከረመ በኋላ መሰከረም 1971 ዓ.ም. ላይ ወደ ፀለምት ሲመጣ፣ የተከዜን ወንዝ ለመሻገር ስንት መከራና ችግር ማለፍ ነበረበት። ተከዜ እስኪጎድል ኤርትራ ውስጥ በነበረው ቆይታ ወቅት በረኀብ የተነሳ የሰንሰል ቅጠል እንደ ጎመን እየቀቀለ ተመግቧል፤ ጋሽ ወንዝ እያላጋ ያመጣውን የግመል ሬሳ ሥጋ በልቶ በተቅማጥ ተሰቃይቷል። ፀሊም ቤቶች የሚኖሩበትን የወልቃይት ቆላ መዚጋ አቆራርጦ ዛሬማ ወንዝን ተሻግሮ፣ በዋልድባ ገዳም አልፎ ጠለምት መምጣት ነበረበት። ከዋልድባ ወደፀለምት ለመሻገር ግን ወደ ተከዜ የሚገብረው የእንስያ ወንዝ የማይበገር ስለነበር፣ ሰውና አጋሰስ የሚያሻግር ከብረትና ሲሚንቶ የተሠራ አነስተኛ ድልድይ ጠለምት ያለው የሪጅን አመራር አዘጋጅቶ መጠበቅ ነበረበት።

ይህ ሁሉ አበሳ ታይቶ ነበር ሠራዊቱ ከመንፈቅ እንግልት በኋላ ጠለምት የደረሰው። ጠለምት እንደደረሰም ደርጉ ወረራ አዘጋጅቶ ጠበቀው። ያንን መመከት የግድ ነበር። ከደርጉ ጋር የሚደረጉት የመከላከል ውጊያዎች እንደተጠናቀቁም፣ የአሲምባውና የጎንደሩ ጦር እንዲዋሐድ ተደረገ በዚያን ዘመን ቋንቋ ተቅሊጥ ይባል ነበር፣ ዐረብኛ ሳይሆን አይቀርም፣ ከኤርትራ ግንባሮች ከወረስናቸው የሽምቅ ቃላቶች መሃል መሆኑ ነው።

## ወልቃይትን እንዳየሁት

የሠራዊቱ ውሕደት እንደተፈጸመ፣ እኔ አዲስ በሚከፈተው ሪጅን አራት ውስጥ ተመደብኩና፣ በመጀመሪያ ቆላወገራን ከጠለምት የሚያገናኘውን መስመር ለማለሳለስ እስከ ጃኖራና አጅሬ ድረስ ተጓዝን። ከዚያም መልስ ወልቃይትን ከኢዴኅና ደርጉ ቁጥጥር ነጻ ለማድረግ፣ ከተማይቱን አዲ ረመጽን ለመቆጣጠር ኦፐሬሽን ተዘጋጀ። ተልዕኮውም በቀላሉ ተፈጸመ። ወልቃይትን ማስተዳደርም ጀመርን። በሥነ ምግባራችን ከኢዴኅ ቀማኛ ሠራዊትም ሆነ ከደርጉ ማዳፋት ተግባር እጅግ የተሻልን ብቻም ሳይሆን፣ የወልቃይት ሕዝብ በመቶ ዓመታት ታሪኩ ሰምቶትና ገምቶት የማያውቅ ሕዝብን አገልጋይ ሠራዊት ስለነበረን፣ ሊወደንና ሊያፈቅረን ጊዜ አልወሰደበትም። ቤቱን፣ ማዕዱን፣ ጎተራውን ከፍቶ በፍቅር ተቀበለን። ፍርሃቱ ጥለነው እንዳንሄድ ብቻ ነበር። የሕዝብ አስተዳደር ኮሚቴዎች እያቋቋምን፣ ወንጀለኛ እየቀጣን፣ ቀማኛ እያደንን በሄድን ቁጥር፣ ፈጣሪ ይህን መልካም አሳይቶ መልሶ አይነሳንም የሚል የመተማመን ሐሳቡን ሕዝቡ ያካፍለን ጀመር።

የኢሕአፓ ተዋጊ ክንፍ የአንዲት አሃዱ ወይም ጋንታ የፖለቲካ ኮሚሳር በመሆን ከጽልዕሎ እስከ ቀፍቲያ፣ ከአዲ ረመጽ እስከ አዲ ጎሹ የሕዝብ አደራጅ በመሆን ከወልቃይት ሕዝብ ጋር ኖሬአለሁ። ከመሶባቸው ተመግቤአለሁ፤ መደባቸው ላይ ተኝቻለሁ፤ በልጆቻቸው ሠርግ ታድሜአለሁ፤ በለቅሶና አንበራቸው ላይ ተቀምጫለሁ። አስተምሬአለሁ፤ ቀስቅሻለሁ። ከኢዴኅ ጋር ሆነው፣ ወያኔን ሲታገሉ ስለከፈሉት መስዋእትነት ሲተርኩ አድምጫለሁ። ‹‹ገዳይ ደደቢት፣ መጠጊያ ድንጋይ በሌለበት›› ብለው ሲፎክሩ ተመልክቻለሁ። ብቻዬንም አልነበርኩም፤ በመቶ የሚቆጠሩ አብረውኝ የነበሩ ታጋዮች ዛሬም በአሜሪካ ይገኛሉ። የትግራይ ልጆች የነበሩም ብዙ ናቸው። እንዲያውም ሕዝብ በማደራጀቱ ሥራ የበለጠ እነርሱ ተመድበው ስለሠሩ፣ የተሻለ መመስከር ይችላሉ። ወደ አሲምባ ካቀናሁበት ከጥር 1969 ዓ.ም. ጀምሮ፣

በትግራይም ሆነ ጎንደር ካየኋቸው በሺህ ከሚቆጠሩ መንደሮች፣ የወልቃይት መንደሮች በሦስት ነገሮች ጉልህ ልዩነት ነበራቸው።

አንደኛው፣ ከፍተኛ የሆነ የቆርቆሮ ቤቶች ከምችት ያሉባቸው መንደሮች ብዙ ነበሩ። በተለይ ከአዲ ረመጽ ወደ ቀፍቲያ መሻገሪያ አቅጣጫ ያሉት መንደሮች፣ እነ ብላምባ ሉቃስና ብላምባ ቅርሺ የመሰሉት ማኅበረሰቦች የሳንቃ ወለል የሌላቸው ከመሆናቸው በቀር፣ በሥርዓት የተገጠሙ የተላጉ በሮችና መስኮቶች ያሉዋቸው፣ የመኝታ ክፍሎቻቸው የተለዩ፣ የቦንዳ አልጋዎች ያሉዋቸውና በዘመናዊ የቤት እቃዎች የሚገለገሉ ነበሩ። ወተቱ፣ ቅቤው፣ እርጎው፣ ጠላው እንደ ልብ ነበር። ሴት ወይዘሮው ንጹሕ የሚለብስ፣ ወንዱ አውቶማቲክ ጠብመንጃ የታጠቀ የጠገበና የኮራ ሕዝብ ነበር።

ለሁለተኛ ጊዜ ተከዜን የተሻገርኩት ከአዲ ጎሹ አካባቢ ወደ ኤርትራ መሻገር በተገደድኩበት ወቅት ነው። ቀኝ እግሬ ላይ መጅ (callus) አብቅዬ መራመድ ተቸግሬ ስለነበር፣ የሠራዊታችን ሐኪሞች የነበሩት ስዕለና መልአኩ ቀዶጥገና አድርገውልኝ ማገገም ላይ በነበርኩበት ወቅት ነበር ወያኔ ወልቃይትን የወረረው። በየቦታው ተበታትነን የነበርን ጥቂት ታጋዮች፣ ከአዲ ረመጽ ወጣ ባለች መንደር ስለወረራው ሁኔታና ሠራዊታችንም የት እንደሚገኝ ከአርሶ አደሮቹ ለማጣራት በምንሞክርበት ጊዜ እዚያ መንደር ውስጥ እንደምንገኝ ወያኔ ስላወቀች አመሻሽ ላይ ታጋዮቿን ልካ በተኩስ አጣደፈችን። ተኩስ በሌለበት አቅጣጫ እያፈገፈግን ተበታተንን። ብላምባ ሉቃስ አድሬ የበለጠ መረጃ ሳሰባስብ፣ አዲ ጎሹ አካባቢ የነበሩት ተዋጊ አሃዱዎች ወደ ኤርትራ መሻገራቸውን አስተማማኝ ወሬ ሰማሁ። ከሌሊቱ በዐሥር ሰዓት ላይ ተነስቼ ገበሬዎቹ ወደቆላ እርሻቸው በሚወርዱበት አሳቻ ቁልቁለት ከደጋው መሬት ወደ አዲ ጎሹ አቅጣጫ ወደሚወስደው በረሃ ወረድኩ። ድንገት የወያኔ አባላት ቢይዙኝ ወደኤርትራ ጠብመንጃ ለመግዛት እንደሚሄድ የጠገዴ ነዋሪ በመንገድ ላይ ትብብር እንዲደረግልኝ የሚያሳስብ ባለማህተም ደብዳቤ ይዤ የኢሕአፓ ሠራዊት አባልነቴን የሚጠቁሙ ቁሶችን በሙሉ አሳዳሪዎቼ ጋ ትቼ ነበር። ከደጋው ወርዶ ሰው የማይኖርበትን በረሃማ ስፍራ ብቻ ይዞ መጓዙ ከፀሐዩ ቃጠሎና ከውኃ እጦቱ ጋር ተዳብሎ መቋቋም የሚቻል አልነበረም። ሆኖም ከዐሥር ሰዓት ያህል የእግር ጉዞ በኋላ ከተከዜ ወንዝ ደረስኩ። ለመጀመሪያ ጊዜም ለላንቃዬ ማርጠቢያ የሚሆን ውኃ አግኝቼ ጠጣሁ። ከወንዙ ማዶ እረኞች ከብቶቻቸውን ሲጠብቁ ተመለከትኩ። ተሻግሬም ተገናኘኋቸው። ኤርትራውያን

እረኞች ነበሩ። በጋይት የሚባሉ ላምና በሬዎቻቸውም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከምናውቃቸው ለየት ያሉና እጅግ የደለቡ ነበሩ።

## አዳር ከኤርትራ እረኞች ጋር

እረኞቹ በረኀብና ጥም መጎዳቴን ሲያዩ በእንጨት ጮጮ ከያዙት ወተት አጠጡኝ። አብሬያቸው አድሬ በበነጋታው መንገዴን ብቀጥል እንደሚሻልና፣ የኤርትራ መንደሮች እስክደርስ የብዙ ሰዓት እግር መንገድ ስለሚቀረኝ ልቸገር እንደምችል ነገሩኝ። በሐሳባቸውም ተስማማሁ። ፀሐይ ከማዘቅዘቋ በፊት ከብቶቻቸውን ወደነፋሻማው ዳገት መንዳት ጀመሩ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ላሞችና በሬዎች በአንድ ላይ ሲታገዱና ሲጠበቁ ሳይ የመጀመሪያዬ ነበር። ወደ በረታቸው የሚያመሩበት ዳገት ለከባድ መኪና የተሠራ ጥርጊያ ይመስል ነበር። ዳገቱን ለአንድ ሰዓት ያህል ከወጣን በኋላ ከከብቶቹ በረት ደረስን። እረኞቹ ከብቶቹን በረት ውስጥ ካስገቡ በኋላ፣ ትልቅ የካምፕ እሳት ማዘጋጀት ጀመሩ። ከተከዜ ወንዝ ዳርቻዎች የሰበሰቧቸውን ጠጠሮች በማሽላ ሊጥ እየጠቀለሉ የሚነደው እሳት ውስጥ ይዶሉ ጀመር። ብርኩታ ተብሎ የሚጠራው እራታቸው እንደሆነ ነገሩኝ። ሆዴ እስኪቆዘር ብዙ ብርኩታ በላሁ።

የምግብ ማብሰያ ብረትድስት ስላልነበራቸው እሳት ውስጥ የጋሙና ፍም የመሰሉ የወንዝ ዳር ጠጠሮችን በመቆንጠጫ ባላ እንጨት እያወጡ አዲስ የታለበው የጮጮ ወተት ውስጥ እያስገቡ ቸስ ብሎ ሲቀዝቅዝ፣ ያንን ጠጠር ወደእሳቱ መልሰው እየወረወሩ ሌላ የጋለ ጠጠር ጮጮው ውስጥ በመጨመር ወተቱ እንፋሎት ማውጣት እስኪጀምር ድረስ እየተቀባበሉ አፈሉት። ከዚያ የፈላው ወተት ላይ የማሽላና በቆሎ ዱቄት በመጨመር ገንፎ አገነፉ። እንዴት እንደሚጣፍጥ ማመን አትችሉም። ገንፎ በልተን እንደጨረስን፣ ከሰው ወደሰው ጮጮው እየተላለፈ፣ አዲስ የታለበ ትኩስ ወተት ፉት ስንልና ስናወራ አምሽተን፣ እዚያው እሳቱ ዳር ተኛን። በጣም ከሩቅ አገር፣ ለሳምንታት ተጉዘው መምጣታቸውንና፣ እስከ ክረምቱ ወራት ድረስም ተከዜ አካባቢ እንደሚቆዩ አጫወቱኝ። በማግስቱ ተሰነባብተን የተከዜን አቀበት መውጣቴን ስቀጥል፣ እነርሱም ትተውት ወደመጡት ተከዜ ለምለም ሳር ፍለጋ ከብቶቻቸውን ይዘው ወረዱ።

## ከኤርትራ ወደ ጠለምት መልስ

ከሁለት ቀናት በኋላ የጀብሃ ሚሊሺያዎች ለአካባቢው የጸጥታ ሹም ለነበረው ለጆርጅ ወስደው አስረከቡኝ። ገና ስንተያይ ከጆርጅ ጋር ኮከባችን ገጠመ። ለዓመታት ተለያይቶ እንደተገናኘ ጓደኛ ማውራትና መከራከር ጀመርን። ስለጀብሀ የማላውቃቸውን ብዙ ነገሮች አጫወተኝ። ለካስ ጀብሃ፣ ተራ የእስልምና አክራሪዎች ድርጅት ሳይሆን፣ በውስጡ የአንጃዎችን መኖር የሚቀበል፣ ከባዚስቶች እስከ ሊብራሎች በአንጃ በአንጃ ተደራጅተው ለጋራ ዓላማ የሚሠሩበት ግንባር ነበር።

ብዞዎቻችን ኢሕአፓ ውስጥ ሳለን ይህን ዴሞክራሲያዊ ገጽታቸውን ፈጽሞ አናውቅም ነበር። ጆርጅ ኤርትራ ከገባችው የኢሕአፓ አሃዱ ጋር አገናኘኝና፣ ወደጠለምት ለመመለስ ተወሰነ። ወልቃይት በወያኔ ስለተያዘ፣ በዚያ ማለፍ የሚታሰብ አልነበረም። እስከ ዛሬማ ወንዝ መገናኛ ድረስ ዋልድባ ገዳም እስክንቃረብ የተከዜን ወንዝ ተከትለን ወደምሥራቅ አቅጣጫ ልንሄድ ወሰንን። ቀኑን ሙሉ ተከዜን ግራና ቀኝ እያቆራረጥን ውለን አመሻሽ ላይ ደከመን። ረኀቡም የሚቻል አልሆነም። መጋቢዎች ከተከዜ ወጥተው ምግብ ፍለጋ ወደመንደሮቹ እንዲሄዱ ታቀደ። ይህን አደገኛ ተልዕኮ የሚፈጽም ፈቀደኛ የሠራዊት አባል ማግኘት አልተቻለም። በመጨረሻ እኔና አንድ ስሙ የተዘነጋኝ የአምባ ማድሬ አርሶ አደር ታጋይ ሄደን ምግብ ለመሰብሰብ ፈቃደኛ ሆንን። አመሻሽ ላይ መንደሩ ውስጥ የወያኔ ጦር አለመኖሩን አጣርተን ገባን። ከነዋሪውም ምግብ እንዲሰበሰብልን አደረግን። ብዙም ሳንቆይ የሕወሓት ታጋዮች መጥተው በተኩስ ያጣድፉን ጀመር። ሁለታችንም ምግቡን ትተን ላለመሸሽና የተኩስ አጸፋ ላለመስጠትም ወሰንን። የተሰበሰበውን እንጀራና ወጥ በነጠላዎቻችን ላይ እያሰርን ተኩስ የሌለበትን አቅጣጫ መቃኘት ያዝን። እንጀራና ወጡን በነጠላችን አስረን ከተሸከምን በኋላ የተኩስ ክፍተት በነበረበት ቀዳዳ ድምጻችንን አጥፍተን ተሰለብን። ወደተከዜ የሚያወርደውን ገመገም ተከትለንም ከጓዶቻችን ተቀላቀልን፣ እራታቸውንም አበላን።

## ስለ ወልቃይት ምስክርነት

ቀደም ብዬ ወልቃይቴ ሀብታም ነው ብዬ ነበር። በሌላው የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል ያላየኸው የተሻለ ሕይወት ወልቃይት ከየት አመጣው ትሉ ይሆናል። ስለ ወልቃይት ስናወራ፣ ወልቃይቴው ማለት ደጋው ላይ የሚኖረው በጽልዕሎ፣ ሽሬላ፣ ደጀና፣ አዲ ረመጽ፣ የብላምባ

መንደሮች፣ ብርኩታና ቀፍቲያ እንዲሁም ቆላው ላይ አዲ ጎሹ የሚኖረው ወልቃይቴ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ በቆርቆሮ ቤቶች በተሻለ ሕይወት መኖር ብቻ ሳይሆን፣ አልፎ አልፎም የእርሻ መኪናዎችም ያሏቸው ጥቂት ባለሀብቶችም ነበሩ፡፡ ቆላ መዘጋው ላይ ከወባና ጊንጥ እንዲሁም ከቆላው ወበቅ ጋር እየታገለ የሚኖረው የፀሊም ቤትና የትግራይ ስደተኛ፣ የደገኛው ወልቃይቴው አገልጋይና ተጠማኝ (share cropper) በመሆኑ፣ ወልቃይቴው መሬት ላይ ከሚያርሰው አዝመራ አካፍሎ የሚኖር ሕዝብ በመሆኑ፣ የደገኛው ሀብት አንዱ ምንጩ ከዚህ ተጠማኝ አራሽ የሚሰበስበው ሰብል ነበር፡፡ የ1966ቱ አብዮት መጥቶ የሁመራ እርሻ ሥራቸው እስኪተንጎል ድረስም፣ የወልቃይት ሰው ሁመራ ላይ የሰሊጥ እርሻ ባለቤት ስለነበር፣ በቅድመ አብዮት ዓመታት ያካበተው ሀብት ብዙ ነበር፡፡ ከሀብታቸው ብዛት እንደ ቀኛዝማች ገብሩ ያሉ ሀብታሞች ሠራዊታችን በሰፈራቸው ሲያርፍ፣ አመራር አባላቱን ጠርተው እንደ እናትና ልጅ ዓይነት ፋብሪካ ውስጥ የተመረቱ መጠጦችን እስከመጋበዝ የሚችሉ ሰዎች ነበሩባቸው፡፡

ሁለተኛው ወልቃይትን ልዩ የሚያደርገው ነገር፣ በየመንደሩ ከፍተኛ የሆኑ የዕድሜ ባለፀጋዎችና፣ ጎንደርና አዲስ አበባን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ገዳሪፍ ወይም ካርቱምን ደጋግመው የጎበኙ ሰዎች በብዛት ይገኙባቸው ነበር፡፡ ብላምባ ሉቃስ ውስጥ የሚኖሩ አቶ ጥላሁን የሚባሉ የቭላድሚር ሌኒን መንታ የሚመስሉ ሰው አንዱ የማስታውሳቸው ነበሩ፡፡ ደጀና ውስጥ የአየር ኃይል አዛዥ የነበሩት የጄኔራል አሰፋ አያና አጎት የሆኑ ግራዝማች መስፍን የሚባሉ ሌላ ምሁርና የታሪክ ሰውም አስታውሳለሁ፡፡ ሁሌም ብዛታቸውና፣ በአንድ በታም ተከማችተው መገኘታቸው ይገርመኝ ነበር፡፡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ጓደኛዬ የነበረው አንዳርጋቸው አያልነህ ስለወልቃይት ሀብትና ወንዳወንድነት (ብረት ወዳድነት) ያወራን የነበረውን ለማመን እንቸገር እንደነበር አስታውስና፣ ኋላ የአንዳርጋቸውን የትውልድ መንደር ቃቃን (በትክክል ካስታወስኩ ከአዲ ረመጽ በእግር የአንድ ሰዓት ተኩል መንገድ ቢሆን ይመስለኛል) ስጎበኝ ከታዘብኩት ጋር ሳመዛዝን፣ ሁሌም ይደንቀኛል፡፡

ሌላው ወልቃይትን ከብዙ ሌሎች ሕዝቦች የሚለየው፣ የዕለት ከዕለትና የሥራ ቋንቋው ከማንነቱ ጋር የተለየ መሆኑ ነው፡፡ በየዕለቱ ወልቃይቴው እርስ በርሱም ሆነ ከተጠማኝ ገባሮቹ ትግሬዎች ጋር የሚገለገልበት ቋንቋ ትግርኛ ነው፡፡ ከፈለገም አማርኛን ይጠቀማል፡፡ ባለ ሁለት ቋንቋ ሕዝብ ነበር፡፡ ሆኖም በትግርኛ ልጁን መዳርም ሆነ፣ ወዳጁ ሲሞትበት በትግርኛ ማልቀስ ግን አይሆንለትም፡፡ የሰርግ ዘፈኑና ለቅሶው፣ ፉከራው፣ ሽለላው፣

የመጫቷ አንቀልባ እሹሩሩ ዜማም ሆነ፣ የፈጪታዋ እንጉርጉሮ አማርኛ ነው። የሚያስገርም የሚያስደምም ኩነት ነው። ወልቃይቴው ትግርኛ ይናገር እንጂ ፈጽሞ የትግራዋይ ሥነ ልቡና የሌለው፣ እራሱን እንደ ኩሩ ጎንደሬ የሚያይ ጅንን ነው። እንዴት ሊሆን ቻለ? ምናልባት ወልቃይቴው ለሕይወቱ የሚያስፈልገውን የምርት ሒደት የሚያከናውኑለት የቆላ መዘጋ ፀሊም ቤቶችም ሆኑ ተጠማኝ የሆኑት የትግራይ ስደተኞችን ለማናገርና ምርቱ ሳይተጓጎል በሰላም ለመጨረስ አስፈላጊ የሆነው የትግርኛ ቋንቋ፣ የዕለት ተዕለት ሕይወቱን ተጽዕኖ አድርጎበት ሊሆን ይችላል፤ ወይስ በሌላ ምክንያት? ምርምርን የሚሻ ጉዳይ ይመስለኛል።

## ወልቃይትና ነጻ የትግራይ ሪፐብሊክ ጥያቄ ትስስር

ወያኔ የነጻ ትግራይ ሪፐብሊክ ማቋቋም ዓላማ በነበረው ወቅት፣ አንደኛ ከውጪው ዓለም የሚያገናኝ መስመር ፍለጋ፣ ከፖርት ሱዳን ወደብ ጋር የሚያገናኝ ወሰን በመፈለግ፣ ሁለተኛ፣ ትግራይ የሦስት ሺህ ዓመታት ሥልጣኔና መሬቱ ያለእረፍት ሲታረስ በመኖሩ ምርቱ እየደከመ የመጣ በመሆኑና በአንጻሩ ወልቃይት/ሁመራ ሰፊ ያልታረሰ ድንግል መሬትና እንደ ሰሊጥ አይነት ካሽ ክሮፕ ሰብል የሚያመርት በመሆኑ፣ ነጻ ለምትወጣው ትግራይ ትልቅ ለም መሬት ስለሚያስገኝ፣ ወልቃይትንና ሁመራን ለመጠቅለል ታቀደ። የሕወሓት መሪዎች ፀገዴ የቢትወደድ አዳነ አገር መሆኑን ያውቁ ስለነበር፣ በትጥቅ ትግሉ ማጠናቀቂያ ዓመታት ክሳድ ግመል ውስጥ ቤዝ አምባ የመሠረቱ ቢሆንም፣ የትግራይ ነው ሲሉ ሰምቼም አላውቅም። በግርግር የጨመሩት መሬት ነው። የትግራይን ነጻ ሪፐብሊክ የማቋቋም ዓላማ ትተናል በሚባልበት ወቅት፣ ወልቃይትንና ጠገዴን ትግሬ የማድረግ ሕልሙ ግን አልቆመም። ለምን?

በ1972 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ወያኔ ወልቃይትን ለመውረር ሲመጣ በመጀመሪያ የኢሕአፓን ጦር መደምሰስ ነበረበት። የኢሕአፓ ሠራዊት ከየሪጅኑ የተውጣጣ ኃይል ሰብስቦ ደባርቅና ዳባት አካባቢ ለመንቀሳቀስ አብዛኛውን ኃይሉን ከወልቃይት ባራቀበት ወቅት ሕወሓት ድንገት ከፍተኛ የሠራዊት ኃይሉን ይዞ ወልቃይትን ወረረ። ከያዘ በኋላ ለማስለቀቅ ቀላል አልሆነም። ብዙ የኢሕአፓም ሆነ የወያኔ የሠራዊት አባላት የተሰውበት የሽሬላና የቆላ መዘጋ ጦርነቶችት የተካሄዱ ቢሆንም፣ ወያኔን ከወልቃይት መንቀል ግን አልተቻለም። እንደገና ወደጠለምት ማፈግፈግ ተገደድን።

ወያኔ ከ1972 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ የወልቃት ይዞታውን ለማጠናከር በከፍተኛ ደረጃ የመሬት ችግር ያለበቸውን ትግሬዎች እያመጣም አሰፈረ። ባለፉት 30 ዓመታት እስከ 80 ሺህ ሕዝብ ከትግራይ አምጥቶ እንዳሰፈረ ይነገራል። አዲስ አበባም እንደገባ ከምዕራባውያን ጋር የሠራዊት ቅነሳ ለማድረግ ሲስማማም፣ ለቅነሳው ማካሄጃ የተሰጠውን ድጎማ በመጠቀም፣ ተቀናሾቹን የወያኔ ሠራዊት አባላት በቀፍቲያና ዳንሻ አካባቢ 30 ሺህ የቀድሞ ወያኔ አባላትን ከነትጥቃቸው አስፍሯል።

ሕወሓት ነባሩን የወልቃይት ሕዝብ በአዲስ ስደተኛ ካጥለቀለቀና፣ መሬት ላይ ያለውን ሐቅ በአመጽ ከቀየረ በኋላ ብትፈልጉ ሕዝበ ውሳኔ (ሪፍረንደም) ይካሄድ፤ ወይም ሲነሽጠው ወደትግራይ ከመጠቅለሌ በፊት ሕዝበ ውሳኔ አካሂጃለሁ ብሎ ያላግጣል። ይህ ግን ተራ ቧልት ነው። ከማንኛውም ሕዝበ ውሳኔ በፊት ወልቃይት ወደነበረበት መመለስና አሁን በቦታው ላይ ያለው የወያኔ የግፍ አገዛዝ መልቀቅ ይኖርበታል። ይህ ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ ስለሕዝበ ውሳኔ ማውራት አይቻልም።

## የተፈጥሮ ወሰን ይከበር

እኔ የአራዳ ልጅ ነኝ። ዛሬ ጊኒር ባሌ ወይም ወለጋ ቄለም የሚኖር የኦሮሞ ወጣት በወያኔ አይዲዮሎጂ ተኮትኩቶ ፊንፊኔ የኔ ናት በሚልበት ወቅት ይበልጥ የሚያንገበግበኝ ጉዳይ ስላለ፥ የወልቃይት ጉዳይ ላይመለከተኝ ይችላል። ሆኖም፣ ሁለቱም ጥያቄዎች የተሳሰሩ ናቸው። የቋንቋ ክልል አይዲዮሎጂ የወለዳቸው። በተጨማሪም የሕይወት አጋጣሚ ሆኖ በፀለምት ወልቃይትና ተከዜ ሽለቆዎች ትዳር መሥርቼ ስለነበር፣ የእማኝ ቃሌን የመስጠት የኅሊና ግዴታ አለብኝ። ተከዜንም ብቻ ሳይሆን፣ ገባሮቹ የሆኑትን ጥራሬን፣ ፍራፍራን፣ እንስያን፣ ዛሬማን ወንዞች ለቀናት ተጉዤባቸዋለሁ፤ አድሬባቸዋለሁ። የጥራሬን ወንዝ የጓዳዬን ያህል አውቀዋለሁ ብል ማጋነን አይመስለኝም። ከወያኔ ጋር ድርጅታዊ ግንኙነት ለማድረግ ከሰቆጣ አካባቢ ተነስቼ አንዲት ቦንብ ወይም አንድ ሽጉጥ ታጥቄ ሙሉ ቀን ወይም ሙሉ ሌሊት ብቻዬን ስጓዝ የጥራሬን ወንዝ ብዙ ጊዜ ተሻግሬአለሁ።

በጥቅምት 1971 ዓ.ም. ከጠለምት ተነስተን ወደ ቆላወገራ ስንሄድና ወደ ወልቃይት ስንመለስ በዛሬማ ወንዝ ዳርቻዎች ለቀናት ኖረናል። የሚበላ እህል ስላልነበር፣ ወንዙ ዳር

የነበሩትን የሸምበቆ ተክሎች እየቆረጥን ከሸምበቆ አገዳ በተሠሩ ቢላዋዎች የሰንጋ ቁርጥ እየጎመድን በዛሬማ ወንዝ ውኃ እያወራረድን በብስናት አልቀናል፡፡ በሰኔ 1972 ዓ.ም. የጠለምት የኢሕአፓ የአርሶ አደር ሚሊሺያዎች ሊከዱ ነው ብለው ጠርጥረውን 13 የሠራዊቱን አባላት ካሰሩን በኋላ ሲነጋ እንዳናገኛችሁ ብለው ሲለቁን፣ ሰኔ 4 ሌሊቱን ሙሉ የፍራፍሩ ወንዝን ግራና ቀኝ ስናቆራርጥ አድረን ከፀሐይ ጋር ቀጠሮ ያለን ይመስል ልክ ስትወጣ ከተከዜ ወንዝ ደረስን፤ ተከዜንም ለሦስተኛ ጊዜ አየሁት፤ ዳግምም ወደትግራይ አቋረጥኩት፡፡ እንኩዋንስ ተከዜ ገባሮቹ እንኩዋ፣ ኃያል ነበሩ፡፡ የተፈጥሮ ወሰኖች፡፡

በእኔ አስተያየት፣ መገናኛና መጓጓዣ አስቸጋሪ በነበረባቸው ዘመናት አንድ ማኅበረሰብ ከዘመዶቹ ርቆ፣ በመሃሉ ከሦስት ወራት በላይ የሚያቆራርጠው ተከዜን ያህል ወንዝ ተሻግሮ ኑሮ የሚመሠርተው አስገዳጅ የሕይወት ገጠመኞች ሲኖሩት ይመስለኛል፡፡ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል ሲልም ሆነ ራሱን ጠብቆ ለማቆየት፣ የሱን ቋንቋ ከሚናገሩ ሕዝቦች ጋር መቆየትን ይመርጣል፡፡ ለዚህም ነው በኢትዮጵያችንም ሆነ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ታላላቅ ወንዞች የሕዝቦች ተፈጥሯዊ ወሰን ሆነው የኖሩት፡፡ በኢትዮጵያም ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም፣ የተራራ ሰንሰለቶች፣ ወንዞችና፣ በረሃዎች ተፈጥሯዊ ወሰን ሆነው የተለያዩ ማኅበረሰቦችን አካልለው በሰላም አኑረዋል፡፡ አሁን ሕወሓት ያንን ዓለማዊ አሰፋፈር ነው በቋንቋ ክልል አይዲዮሎጂ መለወጥ የሚፈልገው፡፡ መልክዓምድር (ጂኦግራፊ) በማኅበረሰቦች አሰፋፈርና ተፈጥሯዊ ድንበር ሆኖ ስለሰጠው ግልጋሎትና ስላደረገው ተጽዕኖ፣ ለመስኩ ባለሙያዎች እተወዋለሁ፡፡ እኔ ግን በዐሥር ዓመት የበረሃ እንግልቴ የታዘብኩት ተፈጥሮ በሕዝብ አሰፋፈር ላይ ያደረገውን ተጽዕኖ ነው፡፡

ይህንን ተፈጥሯዊ የሕዝብ አሰፋፈር ሎጂክ በቋንቋ ክልል ፌዴሬሽን ሎጂክ በመተካት፣ ሕወሐት በጠለምት በኩልም የብራ ዋሰያንና የዋልድባን ለም መሬቶች ከጎንደር በመዝረፍ ከዛሬማ ወንዝ ምላሽ ያለውን አገር በሙሉ፣ ትግርኛ እስከተናገረ ድረስ ትግሬ መሆን አለበት በሚል በጉልበት ወስዷል፡፡ ትናንት ነጻይቱን የትግራይ ሪፐብሊክ በሚመኙበት ሰዓት በወጣትነት ትኩስ አእምሮ የነደፉትን ጨቅላ አስተሳሰብ፣ ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያህል አገር እየገዙ ባለበት ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንደደፈሩ ሳስበው ከወቅቱ ጋር መራመድ ለምን እንደማይችሉና ለምን ከሐቅ ጋር እንደሚላተሙ ሁሌም ይገርመኛል፡፡

አንድ መታወቅ ያለበት ነገር፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣናቸው ከተወገዱ ጥቂት ወራት በኋላ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዴኅ) ሲመሠረት፣ የወልቃይትና ጠገዴ መሳፍንትና የሁመራ ባለሀብቶች፣ ሁመራ ላይ ያገለግሏቸው የነበሩትን ከትግራይ የመጡ የዘመናዊ እርሻ ሠራተኞችን (ወዛደሮችን) አስታጥቀው በደርግ ጦር ላይ ዘመቻ ከከፈቱበት ሰዓት ጀምሮ ላለፉት 40 ዓመታት ከፍተኛ የጦር አውድማ ሆኖ የቆየ አካባቢ ነው፡፡ የታክስ መረጃዎች ተበትነዋል፤ መዝገብ ቤቶች ተቃጥለዋል፤ ታሪኩን የሚያውቁ አዛውንት አልቀዋል፡፡ ወልቃይት ጠገዴ እምብዛም እረፍትና ሰላማዊ አስተዳደር አግኝቶ አያውቅም፡፡ እኔ ወልቃይት በነበርኩባቸው የ1971 እስከ 72 ዓመታት ብቻ እንኳ በእኛና ኢዴኅ መካከል ሥፍራ ሐፀይ አካባቢ፣ በእኛና ወያኔ መካከል በሸሬላና ቆላ መዚጋ አካባቢዎች ውጊያዎች ተደርገዋል፡፡ ወያኔ አካባቢውን ከተቆጣጠረም በኋላ፣ ተገደን ትግሬ አንደረግም የሚለው የትጥቅ ተቃውሞ ቀጥሎ ባለፉት 35 ዓመታት ከፋኝ፣ አርበኞች ግንባር ወዘተ. የሚሰኙ ኃይሎች ከወያኔ ጦር ጋር መቆራቆሳቸውን አላቆሙም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች እካባቢው ተተራምሷል፡፡ የሕወሓት ‹‹ትግርኛ የተናገር ሁሉ ትግሬ ነው›› አይዲዮሎጂ የበለጠ ትርምስና የንብረትና ሕይወት ውድመትን የሚያስከትል ነው፡፡

በእኔ እምነት መፈቀድ የሌለበት፣ ተከዜን ዓይነት የተፈጥሮ ወሰን ተሻግሮ በሌላ ማኅበረሰብ እቅፍ ውስጥ ተጠግቶ የኖረ የወሰን ተጎራባች ሕዝብ፣ ካስጠጋው ሕዝብ መሬት ላይ ቆርሶ በመውሰድም ሆነ፣ ቁጥሩ ከአስጠጊው መብለጡን እርግጠኛ ሲሆን፣ በሕዝበ ውሳኔ ሽፋን ያስጠጊውን ሕዝብ መሬትና አስተዳደር መንጠቅ ሊፈቀድለት አይገባም፡፡

ሆኖም ሕወሓት በሶሻል ኢንጂነሪንግ ስለሚያምን፣ ይህን ሐሳብ አይቀበልም፡፡ በመሬት ላይ ያለውን ሐቅ ስለቀየርኩ ማንም አይነካኝም ብሎ እግሩን አንፈራጦ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ የወልቃይት ጠገዴ ችግር ውሎ አድሮ ኢሕአዴግን ከውስጡ የሚሰረስር ጉዳይ ነው፡፡ እንደ ኦሕዴድ ሁሉ ብአዴንንም ማስሸፈቱ አይቀርም፡፡ የሕዝቡን ጥሪና አቤቱታ ተቀብሎ፣ አማራ ነን በማለታቸው ከሚደርስባቸው መበሳበስና እንግልት ሊታደጋቸው ይነሳ ይመስለኛል፡፡ የብአዴን መፈተኛው ደረሰ መሰለኝ፡፡ ከኦሕዴድ መማር ይችላል፡፡ የወያኔ ተባባሪና መንገድ መሪ ያለመሆን አማራጭ ከፊቱ ተደቅኗል፡፡ በጣም ትንሽ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ የሕወሓት ዓይንና ጆሮ ላለመሆን እንደ ኦሕዴድ መወሰን፡፡ አዎን ይቻላል! (አዲስ ቪዥን - መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም.)

እንሰባሰብ!

ራሳችንን እንጠብቅ!